


የመካነ ደብረሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ህንፃ ከፊትለፊት ሲታይ ።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

# ትንሣኤ



የብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ ከተማ ።

ቁጥር ፻፴፭ የየካቲትና የመጋቢት ፲፱፻፹፩ ዓ·ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብን

ም· አዘጋጅ መ· ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ

አርእስት — ገጽ


ደብዳቤዎች ........ ፩
ጾምና ተግባሮቹ (ርእስ አንቀጽ) ........ ፪
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ........ ፬
ኪዳነ ምሕረት ........ ፯
የስምዖን መታደስ ........ ፰
የጾም ትርጉም ........ ፲
ሰማዕታተ ኢትዮጵያ ........ ፲፩
ዓቢይ ጾም ........ ፲፪
የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ ........ ፲፬
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ ፲፯
የዓድዋ ድል ........ ፲፰
መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ........ ፲፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፳፩
✓ ዜና ሊቃውንት ........ ፳፪
ማረሚያ ........ ፳፬


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታየም ቀጥዬ አንዳንድ ያልገቡኝን ጥያቄዎች እጠይቃለሁ ።

፩ኛ/ የአንድ ሰው ማዕከላዊ ዕድሜው ፶ ዓመት ቢሆንና ከእነዚህም ዓመታት ፵፱ኙን ኃጢአት በመሥራት ከኖረ በኋላ ንስሐ ቢገባና የተቀበለውን ንስሐ ሳይፈጽም ቢሞት ኃጢአቱ ሊሠረይለት ይችላልን ?

፪ኛ/ አንዳንድ ሰዎች ከሃይማኖት ውጭ ሁነው የእግዚአብሔርን ህልውና ይክዳሉ ግን ችግር ሲያጋጥማቸው ወደ ፈጣሪ ተመልሰው አቤቱ አቤቱ እያሉ ይጮሃሉ። እንደነዚህ የመሳሰሉት ሰዎች በመከራ ጊዜ አቤት ቢሉ አቤቱታቸው ይሰማልን ?

፫ኛ/ የትንሣኤ መጽሔትና የድምፀ ተዋህዶ ማኅበረተኛ ለመሆን ይቻላልን ? የሚቻል ከሆነ በትንሣኤ መጽሔት እንድትገልጹልኝ አሳስባለሁ ።

አማኑኤል ተክለ ሚካኤል
ኢትዮ ኢንተርፕረይስስ ከምጥ ንላናት ፋብሪካ

ክፍለ ሀገር ከፋ ጅማ ከተማ
መጽሔቱን ተከታትለህ ቁም ነገሩን አውቀህ ጥያቄ በማቅረብህ እናመሰግናለን ስለ ጻፍክልንም መንፈሳዊ ሰላምታ እኛም መንፈሳዊ ሰላምታችንን እናቀርባለን ። ላቀረብካቸውም ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

፩ኛ/ የአንድ ሰው ማዕከላዊ ዕድሜው ፶ ቢሆንና ፵፱ ዓመት ሙሉ ኃጢአት ሲሠራ ቆይቶ ንስሐ ቢገባ ኃጢአቱ ሊሠረይለት ይችላልን ስለምትለው የሰው ልጅ በተቻለው መጠንና ዓቅሙ በሚፈቅድለት ከኃጢአት መራቅ ተገቢ ነው ። ነገር ግን ሰው ሁኖ የማይበድልና ኃጢአትንም የማይሠራ ስለ ሌለ አውቆ ሳይሆን በስሕተት ኃጢአትን ቢሠራና በሠራው ኃጢአት ተፀፅቶ በንስሐ ቢመለስ የማይሠረይበት ምክንያት አይኖረውም ። መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ተብሎ የተነገረውና የተሰበከውም ኃጢአተኛ በንስሐ እንዲመለስ ነው እንጂ ጻድቃንን አይደለም ንስሐ ግቡ የተባሉት ።

ከዚህም በፊት ኃጢአት ሠርተው አምላካቸውን እግዚአብሔርንም አሳዝነው የነበሩት የቀድሞ ሰዎች በሠሩት ኃጢአት ተፀፅተው እያዘኑና እያለቀሱ ንስሐ ገብተው በደላቸውን ያስደመሰሱ ኃጢአታቸውንም ያስሰረዙና ከፈጣሪያቸው የታረቁ እጅግ ብዙ ናቸው ።

ለምሳሌ አምላክነትን ከመመኘት የሚበልጥ ኃጢአት የለም ነገር ግን የሌለውን አምላክነት የተመኘው የመጀመሪያው ሰው ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱን አስሰርዞ ከፈጣሪው ታርቆ የለምን ? ።

እንደዚሁስ የእሥራኤል መሪ የነበረው ዳዊት በሠራው ኃጢአት ተፀፅቶ ንስሐ ገብቶ ቢያዝንና ቢያለቅስ ኃጢአቱ እንደ ተሠረየለት በመጽ ሳሙ ም ፲፪ ፡ ፲፫—፲፬ ባለው አንቀጽ ተመዝግቦ ይገኛል።

ዋናው ፍሬ ነገር ንስሐ የሚገባ ከተገኘ እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ ለሚቀርቡ እጁን ዘርግቶ ነው የሚቀበላቸው ምክንያቱም መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የቀረበ አምላክ ነውና ።

ንስሐውን ሳይጨርስ ቢሞት ስላልከውም ያው ነው ንስሐ መግባቱና ወደ እግዚአብሔር መመለሱ ነው የሚታየው ራሱ የመጀመሪያውም ሰው ተፀፅቶ ንስሐ ገባ እንጂ ንስሐውን ጨርሶ አልነበረም የሞተው ስለዚህ በሕይወቱ ሳለ የገባው ንስሐ ነው ከኃጢአቱ ነፃ ሊያደርገው የቻለ እና ንስሐውን ሳይጨርስም ቢሞት ከተነሣሐያን የተለየ አይደለም ። ከዚህ ላይ እግዚአብሔር ሰው የሚድንበትን እንጂ ሰው የሚጠፋበትን አይወድም ። ለዚሁም ዋና ማስረጃ ሊሆነን የሚቻለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ኃጢአት በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት ሁለት ወንበዴዎች ከ፵ ዘመናት በላይ የሰውን ገንዘብ ሲዘርፉ የሰውንም ሕይወት ሲያጠፉ ነበር ። ኋላ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል እነዚህ ወንበዴዎች አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ተሰቀሉ ታድያ ያ በቀኝ ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴ አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ብሎ ቢለምነው ወድያውኑ እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ የሚል መልስ እንደ ሰጠው እንጂ ቀጠሮ እንዳልሰጠው ነው የምንመለከተው ሉቃ ፳፫ ፡ ፵፪ ።

ስለዚህ ሰው ኃጢአት ከሠራ

(ወደ ገጽ ፱ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## (ርእሰ አንቀጽ)

# ጾምና ተግባሮቹ

ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፭ ላይ "ከመ ያእምር ጾዋሚ ሕማመ ረኀብ" የሚጾም ሰው የረኀብን ጾር አውቆና ተረድቶ ተርበው ለሚለምኑት ይራራላቸው ዘንድ ነው ይላል ።

ችግርን የቀመሰ ችግርን ያውቃል እንደሚባለው ጾምንም የሚጾም ሰው ረኀብን ፡ ጽምዕን ስለሚያውቅ ለተራቡና ለተጠሙ ሰዎች ያዝናል ። የማይጾም ሰው ግን ረኀብን ስለማያውቅ ለችግረኞች አያዝንም አይራራም ፡ እንዲያውም ረኃብ ምንድን እንደሆነ አያውቅም ።

አንድ ልጅ ከአባቱ ጋር መንገድ ሲሔድ የራበው ሰው ሲለምን አይቶ አባዬ ይህ ሰው ምን እየፈለገ ነው ሲል አባቱን ጠየቀው አባትዮውም እርቦት የሚበላው እየለመነ ነው ቢለው ለምን ኬክ አይበላም ? አለ ይባላል ። ቀደም ሲልም በሊቃውንት ሲነገር የመጣ ታሪክ ለለ ቀጥለን እንመልከተው ።

ጠቢቡ ሰሎሞን አባቱ ዳዊት ንጉሥ ስለነበር ያደገው በድልድል በቅምጥል ነበር ፡ ችግርንም ፈጽሞ አያውቅም ነበር የአባቱን የዳዊትን መንግሥት ተረክቦ ሲያስተዳድር በፍርዱ ትክክለኛነት ሕዝቡ ሁሉ ያደንቁት ነበር ፡ ከዕለታት አንድ ቀን የተራበ ሰው መጥቶ ስመ እግዚአብሔርን ጠራ ፡ ሰሎሞን ምንድን ነው ? ምን ማለቱስ ነው ብሎ ጠየቀ አሽከሮቹም ይህ ሰው ችግረኛ ስለሆነ የሚበላው አጥቶ እርቦት ስጡኝ ብሎ መለመኑ ነው አሉት ሰሎሞንም ረኀብ ምንድ ነው ? በማለት ስለተናገረ እግዚአብሔር ተቀየመበት ወደ ውጭ በሚወጣበት ጊዜ ስመ እግዚአብሔር የተጻፈባት መስጥመ አጋንንት ቀለበት ነበረችው ከዙፋኑ ላይ እንዳለች ረስቷት ወጣ ጽዳት የሚሰጠው ሎሌ ምንጣፉን ሲያራግፍ ከቆሻሻ ጋር ጠርጉ ወደ ወንዝ ጣላት ።

ወዲያው ሰይጣን እሱን ተመስሎ ከዙፋኑ ላይ ተከናነበና ተቀመጠ ሰሎሞን እገባለሁ ሲል የገዛ አሽከሮቹ አትገባም ብለው ከለከሉት እኔ ሰሎሞን እኮ ነኝ አስገቡኝ እንጂ ቢላቸው ሰሎሞንማ ከዙፋኑ ተቀምጦ የለምን ብለው አባረሩት ። ሰሎሞንም በገዛ ከተማው እየለመነ እየበላ ሰባት ቀን ሲንከራተት ሰነበተ ረኀብ ምንድን ነው ብሎ ገፋ ተናግሮ ስለነበር ችግርን ይቀምሰው ብሎ ነው ፡ አንድ ቀን ሰይጣን የሰውን ልብ አስጨክኖበት የሚዘክረው አጥቶ ረኀብ ጸናበት ዓሣ የሚያጠምዱ ሰዎችን ከወንዝ ዳር ስለአየ ሒዶና ለመናቸው እነርሱም የሞተ ዓሣ ወረወሩለት ለካስ የእርሱን ቀለበት ውጦ የሞተ ዓሣ ኑሮ ጠብሶ ለመብላት ሆዱን ቢቀደው ከውስጡ ቀለበቱን አገኛት ። ቀለበቴን ማን አምጥቶ ጥሏት ነው ብሎ ከጣቱ ቢያስገባት ንጉሡ ከዚህ መጥቷል ብለው በዚያ የነበሩ ሰዎች ከበቡት በሕዝብ ታጅቦ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሒዶ ከዚያ በደረሰ ጊዜ ያተከናንቦ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የሰነበተው ሰይጣን ወጥቼ አመልጣለሁ ሲል ስመ አምላክ በመጥራት አጥፍቶታል ።

ይህ ሁሉ ፈተና በጠቢቡ ሰሎምን ላይ የደረሰው ለችግረኛ ባለማዘኑና ረኀብ ምንድን ነው ? ብሎ የማይገባ ቃል በመናገሩ ነው ። ከጾም ጋር የሚሠሩ ብዙ መንፈሳውያን ሥራዎች አሉ ፍቅር ሰላም ፡ ትሕትና፡ ትዕግሥት ፡ ርኅራኄ ፡ ጸሎት ምጽዋት ወዘተ የመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ ከጾም ጋር ሊፈጸሙ የሚገባቸው ምግባራት ናቸው ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ከጾም ጋር ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ሥራዎች ሲናገር እኔ የመረጥኩት ጾም ይህ አይደለምን ይልና የበደልን እሥራት ትፈቱ ዘንድ ፡ የቀንበርንም ጠፍር ትለቁ ዘንድ የተገፉውንም አርነት ትሰዱ ዘንድ ቀንበሩንም ሁሉ ትሠብሩ ዘንድ አይደለምን ፡ እንጀራህን ለተራበ ትቆርስ ዘንድስደተኞችን ድሆች ወደ ቤት ታስገባ ዘንድ የተራቆተውንም ብታይ ታለብሰው ዘንድ ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን ፡

የዚህን ጊዜ ብርሃንህ እንደንጋት ይበራል ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል ፡ ጽድቅህም በፊትህ ይሔዳል የእግዚአብሔርም ክብር በኋላህ ሆኖ ይጠብቅሃል ፡ በዚያን ጊዜ ትጠራዋለህ እግዚአብሔርም ይሰማሃል ትጮኻለህ ፡ እርሱም እቤት ይልሃል" ብሏል ትን ኢሳ ፶፰ ፮—፱ ይኸው ነቢይ ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች እንደደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ ዕንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኋል ፡ የእግዚአብሔር አፍ ይህንን ተናግሯልና ይላል ።



ከደቂቀ ነቢያት አንዱ "ኢዩኤልም" ጾምን ቀድሱ ጉባኤንም አውጁ ሽማግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደአምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ ወደ እግዚአብሔር ጩሁ ሲል አስተምሯል። ት.ኢዮ. ፩.፲፬

በጾም የተጠቀሙ ብዙዎች ናቸው ፡ ጾም ከምግብ መከልከል ብቻ እንዳልሆነ ከላይ ተጠቅሷል ። የጾምን ጠቃሚነት ለማስረዳት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላሳ ዘመኑ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ዕለቱን የሔደው ለጾም ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ነው ። በዚያም ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ጹሟል ። ከዚያም እንዳለ ተራበ በተራበ ጊዜ የሚፈታተነው ሰይጣን ቀርቦ ።

የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ደንጊያዎች እንጀራ ይሁኑ ብለህ እዘዝ አለው ፡ እርሱም መልሶ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው ፡ ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ከተማ ወሰደና በቤተ መቀደስ ጉልላት ላይ አቁሞ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክስ ከዚህ ወደታች ዝለል ወድቂ ብሰበርስ ትለኝ እንደሆነ እግርህ በደንጊያ እንዳይሰናከል ስለአንተ መላእክትን ያዝዝልሃል ተብሎ ተጽፏል አለው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ዳግመኛ ተጽፏል አለው ። ቀጥሎም ዲያብሎስ ረጅም ወደሆነ ተራራ ወስዶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኝ እጅ ብትነሣኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው ። ያን ጊዜ ኢየሱስ ሒድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው ። ወዲያው ዲያብሎስ እንደተቢያ በኖ እንደገም ተኖ ጠፋ ከዚህ በኋላ የሚያገለግሉት መላእክት መጡ ማቴ ፬.፩—፲፩

ሦስት አርእስተ ኃጣውዕ የሚባሉት ስስት ትዕቢት ፍቅረ ንዋይ ናቸው ክርስቶስም በሥስት የመጣውን በትዕግሥት ፡ በትዕቢት የመጣውን በትሕትና ፡ በፍቅረ ንዋይ የመጣውን ሰይጣን በጸሊአ ንዋይ ድል አድርጐ ለእኛም ድል እንድንነሣ አስተምሮናል ጌታችን ይህ አብሮ አደግ ሰይጣን ካልጾማችሁ ካልጸለያችሁ ከእናንተ አይወጣም ብሏል ።

በጾም ማነኛውም በደል እንደሚደመሰስና ወደ እግዚአብሔርም ለመቀረብ እንደሚቻል ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ። ይህ የጾም ወቅት ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ጠላታችን ሰይጣንን ድል የምንነሣበት ስለሆነ ከጾማችን ጋር ጸሎትን ምጽዋትን ትዕግሥትን ትሕትናንና ፍቅርን የመሳሰሉትንም ማዘውተር ይገባናል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የጌታችንየኢየሱስ ክርስቶስንየልደትበዓል ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፡

በከተማና በገጠር የምትኖሩ ምእመናን የወገንን ደኅንነት የአገርን አንድነት በመጠበቅ በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ተሠማርታችሁ በመሐል አገርና በጠረፍ የምትገኙ የኢትዮጵያ ሠራዊትና ሠራተኞች ፡

እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት በደዌ ምክንያት በቤትና በሐኪም ቤት የምትገኙ ሕሙማን ፡

ሕፃን ተወልደ ለነ ፡
ወልድ ተውህበ ለነ ፡
ወቅድመ ኮነ ዲበ መትከፍቱ
ወይሰመይ ስሙ ዐቢየ ምክር
አምላክ ኃያል
አበ ዓለም ፡ ወመልአከ ሰላም

ሕፃን ተወለደልን ወንድ ልጅም ተሰጠን ፡ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ። ስሙም ድንቅ መካር ፡ ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ። ኢሳ. ፱፡፮)

በየዓመቱ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት የምናከብረው የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት የበዓላት ሁሉ መሠረት ነው ።

ቅዱሳን ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ፡ አበው በናፍቆት ይጠባበቁት የነበረው ተስፋ የተፈጸመበት ነውና ። በዚህ ዕለት ወልደ እግዚአብሔር ስለ ዓለም ድኅነት ከሰማያት ወረደ ፡ ቡርክትና ቅድስት ከሆነችው ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወልደ ። በዚህም ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ "ሕፃን ተወለደልን ፡ ወንድ ልጅም ተሰጠን በማለት ቀደም ሲል የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ"።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ በኃጢአት ጨለማ የነበረ ሕዝብ ሁሉ የሕይወት ብርሃንን አየ ፡ ከእግዚአብሔር ርቆና ከክብር ተለይቶ የነበረው ወገን ወደ እግዚአብሔር ቀረበ ፡ ወደ ቀድሞ ክብሩም ተመለሰ ። መንፈሳዊ ነፃነትን ተጎናጸፈ ።

በክርስቶስ ልደት ሰላምና ደስታን ያገኙ የሰው ልጆች ብቻ አይደሉም ። መላእክትም በሰማይ ደስ ብሎአቸዋል ። መላእክት ፡ የሰው ልጅ ከክብሩ በመዋረዱ በመንጸፈ ደይን በመውረዱና በእግረ አጋንንት በመረገጡ ያዝኑ ነበር ። የምህረት በርም በመዘጋቱ ስለ ሰው ልጅ ሲያማልዱ አይችሉም ነበር ። እነሆ ክርስቶስ በመወለዱ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ ፡ ሰላምን አገኘ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሆነ ሰውም ከእግዚአብሔር ጋር ሆነ ። ስለዚህ መላእክት ደስ ብሎአቸዋል ። ለሰውም ምሕረትን ለመለመን የሚወጡና የሚወርዱ ሆነዋል ።

የወልደ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም መምጣትና ሰው መሆን ለሰው ዘር ሁሉ ሰላምን ደስታንና ደኅንነትን አብሥሯል ። ፍርሃትን ጭንቀትንና ጥርጥርን ከሰዎች አስወግዷል ። ስለዚህም ክርስቶስ በተወለደባት ሌሊት መላእክት በቤተ ልሔም አካባቢ በጎቻቸውን ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች "አትፍሩ ለሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ደስታ የሚሆን መድኃኒት ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና" በማለት አብሥረውላቸዋል ። ሰዎችም ይህን የደስታ ቃል ከሰሙና ፍርሃት ከልቡናቸው ከተወገደ በኋላ ከመላእክት ጋር" ስብሐት ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ፡ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" በማለት እግዚአብሔርን አመስግነዋል ።

በመላእክትም ቃል መሠረት ወደ ቤተ ልሔም ሔደው ሕፃኑ ክርስቶስ በጎል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅልሎ አይተው አምላክነቱን [illegible]።

በዚህም እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲህ ወደደ ፡ ዓለም ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን ወደ ዓለም እንደላከው አመኑ ድኅነትንም አገኙ ።

ዛሬም ወልደ እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ወደ ዓለም መምጣቱን አምነው ለሚቀበሉ ሁሉ ገንዘባቸው ነው የዘለዓለም ሕይወት ተዘጋጅቶላቸዋል ። የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንና የሰማያዊ ክብሩን የመውረስ መብት አላቸው ።

"ወደ ወገኖቹ መጣ ፡ ወገኖቹም አልተቀበሉትም ፡ ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" የተባለው አምላካዊ ቃል ይፈጸምላቸዋል ።

የተወደዳችሁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ፡
ካህናት ፡
መእመናን ፡
እንዲሁም በጠረፍና በመሐል አገር የምትገኙ ኢትዮጵያውያን



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሁሉ ፡ የዚህ የተቀደሰው የክርስቶስ በዓለ ልደት የሰላም የደስታና የጤና በዓል እንዲሆንላችሁ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ትጸልያለች ፡ በክርስቶስ ልደት ጊዜ በመላእክት የታወጀው ደስታ ሰላምና አንድነት በዓለም ላይ እንዲሰፍን ቤተ ክርስቲያናችን የሰላም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ትለምናለች ።

ስለዚህ ሁላችንም በዚህ ታላቅ መንፈሳዊ በዓል ዕለት በአንድ ልብና በአንድ አሳብ ሁነን ከመላእክት ጋር ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር እያልን በአሁኑ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ስለሆነው ስለ ሰው ልጅ ሰላም፡ነፃነት፡እኩልነትና አንድነት ልንጸልይና ልንሠራ ይገባናል።

በዝናም ዕጥረት ፡
በመሬት መንቀጥቀጥ ፡
በድርቅና በቸነፈር ተጠቅተው በችግር ላይ የሚገኙትን ወገኖች ሁሉ ልናስባቸው ልንጸልይላቸው በተቻለን ሁሉ መልካምን በማድረግ ልንጎበኛቸው ይገባናል ። ክርስቶስ በቸርነቱ ከአርያም ወርዶ እንደጎበኘ ሁሉ ።

ይልቁንም በዘመናችን በዓለም ሁሉ በሰው ልጅ ላይ ስለደረሰውና መድኃኒት ስላልተገኘለት "ኤድስ" ስለተባለው በሽታ ጉዳይ በጥብቅ ማሳሰብ ዐቢይ የወቅቱ አጣዳፊ ተግባራችን ሁኖ ይገኛል ።

ስለዚህ ቀሳፊ በሽታ መፍትሔ ሁኖ የተገኘው ወንድና ሴት በአንድነት ጸንተው እንዲኖሩ በማናቸውም ኅብረተሰብ የተፈቀደውና የተከበረውን ሥርዓት አጽንቶ መያዝ መሆኑ ታምኖበታል ።

ይልቁንም አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ብቻ የተፈቀደ የሰው ልጅ ጋብቻ በዘመነ ብሉይ የእግዚአብሔርና የሰዎች ግንኙነት ምሳሌ ሲሆን ዘፍ.፪.፳፬ ። ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባልና ሚስት ሁለቱ አንድ አካል ናቸው ሲል የመጀመሪያውን ሕግ አጽንቶ ቃል ማቴ.፲፱.፫—፭ ይህን አምላካዊ ቃል መመሪያ አድርገው የሰው ልጆች የኑሮ ደረጃ ጤንነትና ክብር የተስተካከለ እንዲሆን የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች በየጊዜው አስተምረዋል ።

አንደኛ ጢሞ.፫.፪—፬ ፡

እኛም በዚህ የሰው ልጆች ሰላም ጤንነትና ነፃነት እኩልነት የተገኘበትን የክርስቶስን ልደት በምናከብርበት ወቅት ሁሉ እነዚህ በክርስቶስ የተመሠረቱ የሰው ልጆች የኑሮ ሀብት የሆኑ ሁሉ በሰው ልጆች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን በየጊዜው ማስተላለፍ የቤተ ክርስቲያናችን የዘወትር ተግባር መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን ።

እንግዲህ ይህን ታላቅና መንፈሳዊ በዓል ስናከብር የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ትህትና በልደቱ ለሰው ዘር የተሰጠውን ልዕልና ነፃነት ሰላምና አንድነት ማሰብ ይገባናል ። ስለህ





www.ethiopianorthodox.org

# ኪዳነ ምሕረት

ኪዳን የሚለው ቃል ተካየደ ተማማለ ተስማማ ፡ ውል ገባ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው ። ኪዳነ ምሕረት ማለትም የምሕረት ቃል ኪዳን ማለት ሲሆን መድኃኒታችን ክርስቶስ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ስለሰው ልጆች ይቅርታ የገባላት ቃል ኪዳን ነው ።

እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሁሉ በተለያዩ ጊዜያት ብዙ ኪዳናትን ሰጥቷል ። የሰው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ በሄዱ ቁጥር ኃጢአታቸውም እንዲሁ እየበዛ በመሄዱ በውሃ ሥጥለቅለቅ እንዲጠፉ ባደረገ ጊዜ ኖኅ የተባለው ሰው ጻድቅ ስለነበረ የሚድንበት መርከብ እንዲሠራ አዘዘው ። ኖኅም እንደታዘዘው መርከብ በየወገናቸው ተባዕትና አንስት በየወገናቸው እየሆኑ በመርከብ ውስጥ ገብተው እንዲድኑ አደረገ። የጥፋት ውሃም ካለፈ በኋላ እንደገና እንዲበዙና ምድርን እንዲሞሏት እግዚአብሔር ኖኅን አዘዘው ። ምድርንም ዳግመኛ በውሃ እንዳያጠፋት ቃል ኪዳን ገባለት። ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር ። በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቴ በደመናው ትታያለች በእኔና በእናንተ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ ዘፍ.፱፡ ፲፫—፲፰ ይህም ቃል የጸና ሆኖ ምልክቱ (ቀስተ ደመናው) እስከ ዛሬ ድረስ በግልጥ ሲታይ ይኖራል ።

ቀጥሎም አብርሃም ልጅ ባለመውለዱ እያዘነ ሲኖር ከእለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ተገለጠ



ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

አብርሃም ሆይ አትፍራ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው” አለው እሱም አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ ምን ትሰጠኛለህ ዘር አልሰጠኸኝም ወራሼም የለኝም ባለው ጊዜ ልጅ እንደሚወልድ ዘሩም ከሰማይ ከዋክብት ከምድር አሸዋ እንደሚበዙና ከግብፅ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ያለውን ምድር ለዘሩ እንደሚያወርሰው ቃል ገባለት አብርሃምም አምኖ ተቀበለ እንዲሁም ተፈጸመለት ዘፍ.፲፭ ፩—፯

እንደዚሁም በነቢዩ ዳዊት አፍ ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ (ከመረጥኋቸው ከወዳጆቼ ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ) ካለ በኋላ ለእርሱም የሰጠውን ቃል ኪዳን እንመለከታለን ይኸውም ዳዊትን ከሌሎች ወገኖች አብልጦ ከመረጠውና የብዙ ወገኖች መሪ አድርጎ ባስቀመጠው ጊዜ ዳዊት ልበ አምላክ ከመባል ድረስ ለፈጣሪው ቅን አገልጋይና ፍጹም ታማኝ በመሆኑ” ለአገልጋዩ ለዳዊት ማልሁ ዘሩንም ለዘለዓለም አጸናለሁ” ብሎ ምሎለታል መንግ አጸናለሁ” ብሎ ምሎለታል ። ዘሩንም ለዘለዓለም አጸናለሁ ማለቱም ለጊዜው ለልጁ ለሰሎሞን ይሁን እንጂ ኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሱ ዘር ከምትሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ማዳኑን ሲያስረዳ ነው ። ይህም አዳም በፈጸመው በደል በተጸጸተ ጊዜ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ የሚል ቃል ኪዳን ገብቶለት ስለነበር ጊዜው ሲደርስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ትንቢቱም እንደተፈጸመ ያረጋግጣል ።

ኋላም መድኃኒታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳለ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ) በዚያ ስለነበር እናቱ ድንግል ማርያምን ያጽናናት ዘንድ” ነዋ ወልድኪ እነሆ ልጅሽ ወነያ እምከ እናትህ እነኋት” በማለት አደራ ሰጥቶታል ዮሐ ፲፱፡፳፯ ዮሐንስም እመቤታችንን ወደ ቤቱ ወስዶ ካስቀመጣት በኋላ በየቀኑ እየሄደች በልጇ መቃብር ላይ በጎልጎታ ትጸልይ ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን እንደተለመደው ስትጸልይ ልጇ ክርስቶስ አእላፍ አእላፋት መላእክትን አስከትሎ ወደ እርሷ በመውረድ” ስምሽን የጠራ ቤተ ክርስቲያንሽን የሠራ በስምሽ የተራበ ያበላ ፡ የተጠማውን ያጠጣ የታረዘ ያለበሰ ፡ ያዘነ ያረጋጋ ወይም ውዳሴሽን ያጸፈ ሴት ልጅንም ሆነ ወንድ ልጅን በስምሽ የሰየመ ሁሉ እምርልሻለሁ ሲል ቃል ኪዳን ገብቶላታል ። የእርሷም ልመናዋና ጸሎቷ ስለሰዎች መዳንና መመለስ ስለነበር አመስግና ተቀብላለች ይህም በጸሎት ድኅነት መገኘቱን ያስተምረናል ።

ይህንንም ቃል ኪዳን የተቀበለችው ከክርስቶስ እርገት በኋላ የካቲት ፲፮ ቀን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኑዋ ባለበት ቦታ ሁሉ በታላቅ ድምቀት ሲከበር ይኖራል ይህም ዕለት ከእመቤታችን ታላላቅ በዓላት አንዱ በመሆኑ ምእመናን ሁሉ በደስታና በተስፋ መታሰቢያዋንም በማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን ክርስቲያናዊ ተግባራት በመፈጸም ማክበር ይገባናል ።

ለእርሷ የተሰጠው ቃል ኪዳን ለመላው ምእመናን ስለሆነ በእርሷ አማላጅነት ያገኘነውን ተስፋ ለመቀበል እኛ ደግሞ ለተጐዱትና ተስፋ ለሌላቸው ወንዶሞቻችን እንዲሁ አዛኞችና ርኅሩሆች መሆን ይፈለግብናል እንዲሁም ስሟን በመጥራት ብቻ እንድናለን በማለት ከሕግ ውጭ በምንፈጽማቸው ተግባሮች የምንጠየቅባቸው መሆኑን መዘንጋት የለብንም ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ተወልዶ ዓለምን በማዳኑ መድኃኔ ዓለም ተብሏል እርሷም የዓለም ድኅነት መገኛ በመሆኑዋ ቤዛዊተ ዓለም ተሰኝታለች ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ልናመስግናት ፡ ልንሰግድላት ፡ ልናከብራትና ልናገናት ይገባናል። ዛሬ በአፀደ ሥጋ ያለነው ብቻ ሳንሆን በእርሷ ተማጥነው በአማላጅነቷ ድነው በአፀደ ነፍስ ያሉት ነፍሳትም አንቺን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና ይድርሰው ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው በመሆን በአንቺ ምክንያት የዘለዓለም ሕይወትን አግኝተናልና እያሉ ሲያመስግኑዋት ይኖራሉ ።

ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ጠብቀውና አክብረው ያለፉ ቅዱሳን አባቶቻችን የዘለዓለም ክብርን እንዳገኙ ሁሉ እኛም ቃሉን ብንጠብቅ ይጠብቀናል ፡ ብናከብረው ያከብረናል ። ነገር ግን የእግዚአብሔርንም ሆነ የድንግል ማርያምን ስም በመጥራትና በመሐላ የተዋዋልነውን ቃል ኪዳን የምናፈርስ ፡ በሐሰት የምንመሰክር በአድልዎ የምንናገር በጥቅም ተደልለን ሌላውን የምንጐዳ ከሆነ የተሰጠነውን ቃል ኪዳን ዘንግተናል የምንፈልገው ሞተ ሥጋንና ሞተ ነፍስን እንጂ ድኅነተ ሥጋንና ድኅነተ ነፍስን አይደለም” የማይረባውን ቃል ይናገራሉ ቃልኪዳን በገቡ ጊዜ በሐሰት ይምላሉ ። ስለዚህ በእርሻቸው ላይ መርዛም ሣር እንደሚበቅል መቅሠፍት ይበቅልባቸዋል” ሲል ነቢዩ ሆሴዕ ምዕ.፲ ቁ.፬ እንደተናገረው በምሕረት ፋንታ መቅሰፍትን ፡ በሥርየት ፋንታ መረገምን የምናመጣ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባናል ።

መድኃኒታችን ክርስቶስ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው ለሐጥአን ሊፈርድባቸው በክብር ዙፋን ላይ በፍርድ በተቀመጠ ጊዜ የሚጠይቀው ተርቤ አብልታችሁኛልና ፡ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ፡ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ፡ ብታረዝ አልብሳችሁኛልና ብታመም ጠይቋችሁኛልና እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ ኑ ብሎ ይጠራቸዋል ። እነዚህም ከላይ የተዘረዘሩትን ለችግረኞች ላደረጉ በቃል ኪዳኑ ጸንተው ሕጉን ጠብቀው የኖሩ

ገራችን አንድነትና ሰላም ዕድገትና ብልጽግና በቃልም በተግባርም መግለጽ የሁላችንም ዓላማ መሆኑን መርሳት የለብንም ።

ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ፡ አሜን ገላ.፩ ፡ ፬





www.ethiopianorthodox.org

# የስምዖን መታደስ

ይህ ሰው ረጅም ዘመናት ለሀገር መልካም ሥራ በመስራቱና ለወገንም ቅን አገልግሎት በማበርከቱ ተሀድሶ እንዳገኘ ከራሱ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ታሪኩም እንደሚለው ካሕኑ ስምኦን ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለት መቶ ዓለም በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት መጻሕፍተ ብሉያት ተሰብስበው ከእብራይጥስ ወደ ግሪክኛ በሚተረጎሙበት እየታረሙ ተቃንተው በሚሻሻሉበት ጊዜ ከሰባው ሊቃናት መካከል አንዱ እንደነበር ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ። በሙያው በኩል ቢሆን የብሉያት ትርጓሜ መምሕርና የአይሁድ ሕግ አዋቂ መሆኑንና ቁም ጸሐፊ እንደነበር ከራሱ የሕይወት ታሪክ ለማወቅ አስቸጋሪ አየሆንም ።

ከዕለታት በአንደኛው ቀን መጽሐፈ ኢሳይያስ ምዕ ፯ ቁ ፲፬ ሲጽፍ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ከሚለው ሲደርስ ነገሩ ስለከበደውና በመንፈስም ስላልተገለፀለት ድንግል የሚለውን ፍቆ አንዲት ልጅ ትፀንሳለች ሲል ጻፈ መልአኩም ይህንን ፍቆ ድንግል ብሎ ጻፈበት እንደገናም መልሶ ሲፍቅ ለሁለተኛ ጊዜ መልአኩ ድንግል ትፀንሳለች ሲል ጽፎ አገኘው ስምዖንም ቀድሞውንም ኢሳይያስ የተናገረው በመንፈስ ቅዱስ እየተመራና አሁንም ጽሑፉ የተፋቀው በፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን አመነ በዚህ ጊዜ ስለስህተቱ እያዘነና እየተፀፀተ ይህ ሥራ ከሚፈፀምበት ዘመን ደርሶ የምትፀንሰውን ድንግል እንዲያይና ከእርሷም የሚወለደውን መሲህ እንዲመለከት እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ እንዲሰጠው ጸሎቱን ሐዘኑን ናፍቆቱን ጭምር ወደ ፈጣሪው ጠዋት ማታ ያቀርብ ጀመር ብዙ ሐብት አግኝቶ ከሚከበር ይልቅ ይህንን ቢያይ የሚከብርና የመንፈስ ዕረፍት የሚያገኝ መሆኑን ስለተረዳ ሐሳቡንም ምኞቱንም ወደዚሁ አዘነበለ ።

ስምኦን ይህን ሁኔታ ሲጠባበቅ አረጀ ሸመገለ በእርጅናው ወራት ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወለደ በስምንተኛውም ቀን የግዝረት ሕግ ተፈፀመለት በልማዱም መሠረት አርባ ቀን ሲሞላው እናቱ ማርያምና ጠባቂው ዮሴፍ መስዋዕት ይዘው በኢየሩሳሌም ወደ ሚገኘው ወደ ታላቁ ቤተ መቅደስ ሕፃኑን ኢየሱስን ወስደው በእግዚአብሔር ፊት አቆሙት ሽማግሌው ስምኦንም በመንፈስ ቅዱስ ወደ ቤተ መቅደስ ወጣ የጸሎቱና የሥን ሥርአቱም ተካፋይ የመሆን ዕድል አገኘ።

ሕፃኑን ክርስቶስንም ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተቀብሎ አቀፈው ። በዚህ ጊዜ አርጅቶ የነበረው ስምኦን ታደሰ ። ከዘመኑም ደርሶ ሕፃኑንና እናቱን በማየቱ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ይህም ሰው ጻድቅና ትጉህ ከመሆኑም ባሻገር የእስራኤልን መፅናናት ይጠባበቅ ስለነበር የተወለደውን ሕፃን ማየት ብቻ ሳይሆን ከእናቱ ተቀብሎ በማቀፍ በክብር ላይ ክብር በፀጋ ላይ ፀጋ ተጨመረለት ፡

በተሰበሰበውም ሕዝብ መካከል እንዲህ ሲል መስክረ ። ጌታ ሆይ እንደቃልህ አገልጋይህን በሰላም ታሰናብተዋለህ አይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ሲሆን ለሕዝብም ለእስራኤል ክብር ነው ። ይህም ለሚያምኑና ለሚከተሉት እስራኤላውያን መነሻቸውና ከፍ ከፍ እያሉ መንፈሳዊ እድገት የሚያገኙበት ሲሆን ለማይከተሉትና ትምህርቱን ለሚቃወሙት ደግሞ መውደቂያቸው ነው" አለ ሉቃ ፪፡፳፭ ፴፪ ይህንም በመናገሩና ሕፃኑን ክርስቶስን በማቀፉ ከእርጅናው ታድሶ አዲስ ሰው ሆኖአል ።

እንግዲህ ስምኦን ከእርጅናው ታደሰ ሲባል ምን ማለት ነው? ብዙ ፍጥረቶች ሲታደሱ እናያለን። ከነዚህም መካከል ንስርን ብንጠቅስ ካረጀ በኋላ የክንፉ ላባ ፀጉሩ ሳይቀር ተነቃቅሎ በአዲስ ላባና ባዲስ ፀጉር ተለውጦ እንደገና ይታደሳል ስለዚህም ነቢዩ ዳዊት በመዝ ፩፻፪ ቁ ፩" በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት ጐልማሳነትነትሽን እንደንስር ያድሳል" ብሏል ኢሳያስም በበኩሉ በም ፵ቁ ፴፩ ስለመታደስና ኃይል ስለማግኘት ሲናገር" እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደንስር በክንፍ ይወጣሉ ይሮጣሉ አይታክቱም ይሄዳሉ አይደክሙም" ብሏል የሁለቱም አነጋገር ጐልማሶች ሥጋዊ ኃይል በሥራ ታድሰው ትኩስ ኃይል አዲስ ጉልበት አግኝተው ፈጥነው የሚሠሩ መሆናቸውን ከመግለፃቸውም ሌላ ሩጠው የሚቀድሙ ሠርተው የማይደክሙ መሆናቸውንና ስለ ሥጋ ተሐድሶ ተናገሩ እንጂ ስለ መንፈስ ተሐድሶ እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል ይህም ከስምኦን ተሐድሶ ጋር የተለያየ ነው። የሥነ ፍጥረት ሊቃውንት እንደሚሉትም ቢሆን እባብም ይታደሳል በክረምት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ሳይወጣ ከእዚያው እንዳለ ይከርማል ክረምት አልፎ ፀሐይ ሲወጣ መሬቱን ሙቀት ሲሰማው ብርሃኑ ሲያንፀባርቅ ያረጀው ቆዳ ተገፎ ይወድቅና አዲስ ቆዳ ይለብሳል ይህም በተፈጥሮው ያገኘው ጸጋ ነው እባብ አዲስ ቆዳ ቢለብስም መንከሱንና መርዙን የማስረጨት ክፉ ጠባዩን ለውጦ እንደቆዳው አዲስ ጥሩ ጠባይ አይለብስም ያንኑ የአውሬነቱን ጠባይ እንደያዘ ይኖራል ። የስምኦን ተሐድሶ ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው ይህም ማለት ያረጀ ቆዳው ተገፎ በአዲስ ቆዳ አልተለወጠም አዲስ አካልም አለበሰም እንደጐልማሶችም አዲስ እግር አግኝቶ አልሮጠም ማንንም አልቀደመም ከሽምግልናም ተለውጦ የ፴ ዓመት ጐልማሳ አልሆነም መዝሙረኛው ዳዊት ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አዲስ ሲል እንደተናገረው ሽማግሌው ስምኦን ንጹህ ልብ ተፈጠረለት የቀናውም መንፈስ በሕይወቱ ውስጥ አደረበት ካሮጌ ሕይወትም ወደ አዲስ ሕይወት ተለወጠ የመንፈስ ለውጥም አገኘ በዚህ ጊዜም አዲስ ሰው ሆነ የስምኦን ለውጥ ይህን ይመስል ነበር ።

ይህን መሳዩ ተሐድሶ ክርስቲያኖችም ያስፈልጋቸዋል የተሐድሶ ዓይነቱ ብዙ ነው ሰው በየተሰማራበት ሥራ ያስፈልገዋል ሥራውንም ራሱንም አዲስ ማድረግ ያሻዋል ። ሠራተኛውም በሐሳቡና በእንቅስቃሴው በትጋቱ ደካማና ያረጀ ከሆነ የሚሠራውም ሥራ እንኳንስ አልፎ ተርፎ ወገንን ሀገርን ቤተ ክርስቲያንን ሊረዳ አይችልም።

ስለዚህ ከአረጋዊውና ከነቢዩ ስምኦን የምንማረው ብዙ ትምሕርት አለ ይኸውም ለወገኖቹ መፅናናትን እና ለሥራ መነሳታቸውንና ከፍ ከፍ ማለታቸውን የሀገሩ ተቃዋሚዎች ደግሞ መውደቃቸው በመጨረሻም ይህንን ሁሉ ለማድረግ በሰላም የሚመጣውን ክርስቶስን ሳያይ እንዳይሞት ይመኝ ነበር ምኞቱም እንደተፈፀመለት ተመልክተናል እኛም የመንፈስ ተሐድሶ አግኝተን ርስተ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንድንችል እንደአረጋዊው ስምዖን ጸሎታችንና ልመናችን ሁሉ ከንጹህ ልብ እንዲሆን አምላካችን ይረዳን ዘንድ ዘወትር እንለምነው ።

ወ/ት መአዛ አስማማው።

---

ጻድቃን ናቸው እነዚህን ፈጽመው ላልተገኙ ኃጥአን ግን ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀው የዘለዓለም ኩነኔ ሂዱ ብሎ እንደሚያሰናብታቸው ቅዱስ ወንጌል በሰፊው ያስረዳል ማቴ ፳፭ ፴፩. ፴፮፡

በዚህ ዓለም እርስ በእርሳችን የምናደርጋቸው ውሎችና ቃልኪዳኖች ፈርሰው ቢገኙ ውል አፍራሽ ወገን በሕግ ፊት ቀርቦ በመረጃ ሲረጋገጥበት ቅጣቱን ተቀብሎ ውላቸው የጸና እንደሚሆን ፡ ከእግዚአብሔርም የተቀበልነውን ቃል ኪዳን አፍርሰን ከተገኘን የሠራናቸው ክፉ ሥራዎች መረጃ (ምስክር) በመሆን ያስፈርዱብናል ። የእግዚአብሐር ቃል ግን ለዘለዓለም የፀና ሆኖ ይኖራል።

ስለዚህ ቃሉን ጠብቀን በሕጉ ፀንተን በመኖር በክርስቶስ ይቅር ባይነት በእመቤታችን ድንግል ማርያም አማላጅነት ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንድንወርስ መልካም ፈቃዱ ይሁንልን ።

መ/መንክር ዋሴ

---

## ደብዳቤዎች

(ከ፩ኛ ገጽ የዞረ)

በኋላ ንስሐ ከገባ ኃጢአቱ እንደሚሰረይለት አትጠራጠር ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ምሥጢረ ንስሐን የሠራልን በማየ ንስሐ ታጥበን እንድንነጻና ካለብን የኃጢአት እድፍ ነጻ እንድንሆን ነው ። በበለጠም ለመረዳት እንድትችል የማቴዎስ ወንጌል ምዕ ፲፰ ፡ ፩ እስከ መጨረሻ ብትመለከት መልካም ነው ። ፪ኛ አንዳንድ ሰዎች ከሃይማኖት ውጭ ይሆኑና የእግዚአብሔርን ሀልውና ይክዳሉ ግን አንድ ችግር ሲያጋጥማቸው ወደ ፈጣሪ ተመልሰው አቤት አቤት ይላሉ ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ክደው እንዴት በአንድ ጊዜ ኃጢአታቸው ሊሠረይላቸው ይቻላል ስለምትለውም ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር የሚፈልገው ሰው ሁሉ ከኃጢአቱ ተመልሶ ወደ እርሱ የሚመጣውን ስለ ሆነ መመለሱን ብቻ ነው የሚፈልገው ።

፫ኛ/ የትንሣኤ መጽሔትና የድምፀ ተዋህዶ ጋዜጣ ማኅበርተኛ ለመሆን የሚቻል ከሆነ እንድትገልጹልኝ ስለምትለውም ።

ለመጽሔትና ለጋዜጣው የሚከፈለውን ገንዘብ ከከፈልክ ማኅበርተኛ ለመሆን ትችላለህ ። እንዲ

(ወደ ፲፩ ገጽ ዞሯል)





www.ethiopianorthodox.org

# የጾም ትርጉም

ገና ከመጀመሪያው የሰው ዘር አኗኗር ሥርዓት ሲታይ ከአንድ ዓይነት ምግብ መከልከል ወይም መጾም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የአዛዥነትና የታዛዥነት መታወቂያ ሆኖ የተሠራ ተቀዳሚ መንፈሳዊ ሕግ መሆኑን ከዚህ የሚከተለው መጽሐፋዊ ጥቅስ ያስረዳል። "እግዚአብሔር አምላክ በአርአያውና በምሳሌው የፈጠረውን ሰው "ክፉና በጎውን ለይቶ ለማወቅ ከሚያስችል በገነት መካከል ካለው ዛፍ ፍሬ እንዳትበላ ተጠንቀቅ ከርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ብሎ አዘዘው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ቃለ ትእዛዝ መሠረት ጾምና ጸሎት ሳይነጣጠሉ የሥርዓተ ኑሮና የሥራ መጀመሪያ ሆነው እናገኛለን። ለማስረጃም ያህል ሙሴ ፵ መዓልትና ዓርባ ሌሊት ጾሞ ሕገ ኦሪትን (አሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበትን ጽላተ ሕግ) ለመቀበል በቅቶአል። ይህም ምሳሌ ሆኖ ሲሠራበት ቆይቶ በማዕከለ ዘመን ክርስቶስ የሰውን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ በተዋሕዶተ ሥጋ በተገለጠ ጊዜ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ከምግብ በመከልከል ለእኛ አብነት ለመሆን የሥራው ሁሉ መጀመሪያ አድርጎታል (ማቴ ፬·፪—፲፩)።

ቀዳማይ አዳም በምግብ ተፈትኖ በመውደቁ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ። ዳግማይ አዳም ክርስቶስ ግን በምግብ ሳቢያ የመጣበትን ፈተና ሁሉ በጾም ድል ነሥቶ የጽድቅ ጠላትና የሐሰት አባት የሆነውን ዲያብሎስን አሳፍሮ መለሰ።

እነሆ ያ በገነት ተክሎች መካከል ከዕፀ ሕይወት ጐን የነበረው "ክፉውንና በጎውን ለይቶ የሚያሳውቅ" ተብሎ የተጠራው ዛፍ በመላው ዓለም ላለው የክፉ ሥራ ሁሉ ምንጭ ምሳሌ ነበር። ቀዳማይ አዳም ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ለመብላት ሳይመኝ በተለይ ክፉና በጎውን ለይቶ ያሳውቃል ከተባለው ዕፀ ፍሬ ለመብላት የጐመጀበት ምክንያት ፍሬው ከሌሎች ዕፀዋት የሚበልጥ ሆኖ አይደለም። አትብላ "ተብሎ በመታዘዙ ብቻ" ስለምን? የሚያሰኝ ጥያቄ ያሳደረበት ይመስላል። በዚህም ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ይልቅ የጠላት ምክር እንዳሸነፈው ያሳያል።

ከዚህም አንፃር ሲታይ ከሰው ዘር ሁሉ መካከል አንዳንዱ "ይጐዳሃል፤ አታድርግ፤ (ኢትጥአም፤ ኢትልክፍ አትንካ) ያሉትን ነገር ሁሉ ለማድረግ እንደዚህ ያለ ብርቱ እልህ እንዳለበት እናያለን። ለምሳሌም ዛሬ በዓለም ላይ ለብርቱ ሱስ የሚዳርጉ አደገኞች ዕፀዋት የሐሺሽና የጠንካራ አልኮሆል ብዛት ምን ያህል የሕይወት ጠንቅ እንደሆነ የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች በቃልም፤ በጽሑፍም ሲያውጁለት የሚኖር ሲሆን የሰው ፍላጐት ይበልጥ እየጠነከረ መምጣቱ በብርቱ የሚያሳዝን ነው። በሌላም በኩል ይህን ሁሉ ምክር የሚለግሱት ሐኪሞች አንዳንዶቹ ከዚህ ችግር ነፃ ሆነው አለመገኘታቸው ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ነው።

"ዋጥ ስልቅጥ ነው ጂን አይላ መጥም
ጉበት ዘመድ ላይሆን አልለማመጥም።"

በማለት በገዛ ሕይወታቸው ላይ ሞት የሚፈርዱበት እጅግ ብዙ ናቸው።

እነሆ ፍሬው እንዳይበላ በተከለከለው በዚያ ዕፀ በለስ ጥላ ሥር ሞት ተደብቆ በስተጀርባ ያደባ ነበር። ነገር ግን ቀዳማይ አዳም ከተፈጥሮ በተሰጠው ግዕዛን አእምሮ በምግብ የመጣበትን ፈተና ሳይገነዘብ ቀረ።

ያም ሞት የነፍስ ከሥጋ መለየት ጉዳይ ሳይሆን በተለይ ከእግዚአብሔር ቤተሰብነት የመራቅን ሁኔታ ያመለክት ነበር። ይህንም ሊቁ ቅ/ቄርሎስ በድርሳኑ ሲገልጥ "ሞታ ለነፍስ ርሒቅ እም እግዚአብሔር" የነፍስ ሞትዋ ከእግዚአብሔር መራቅ ነው" ሲል ተርጉሞታል።

ባጠቃላይ የተከለከለ ምግብን ተከትሎ የሚመጣ ፈተና ምን ጊዜም ቀላል ሆኖ አያውቅም ለማስረጃ ያህል ዔሣው ከአንድ ጊዜ ለማያልፍ ምግብ፤ ያውም ለምሥር ንፍሮ ብኩርናውን እስከ መሸጥ ደርሶአል። ያንንም ያጣውን ብኩርና እንደገና መልሶ ለማግኘት ያፈሰሰው ዕንባ የሸረበው ደባ ምንም ውጤት አላስገኘለትም። (ዕብ·12 ·16)

እንዲህ ያለው ምግብ ጠቀስ ፈተና በአንዳንድ ግለሰቦች ብቻ የሚወሰን አይደለም። ከብሔር አቀፍ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ብሎ ሕዝብና አሕዛብን ሁሉ በጅምላም ሆነ በተናጠል ሲፈታተን የኖረ ነው እንጂ። ለምሳሌም ያህል ታሪክን ስንመለከት በእስያ፡ በአፍሪቃና በላቲን አሜሪካ ከሚገኙት በርካታ አህጉር መካከል አንዳንዶቹ ከቅኝ ገገሮች የቀረበላቸውን መደለያ እጅ ነሥተው ለመቀበል ሲያጐነብሱ ክብረ ኅሊናቸውንና በዋጋ የማይገኝ ነፃነታቸውን ከማጣት ደረጃ መድረሳቸው ይነገራል። ይህም ሁሉ ታሪክ እኛ ልንመከርበትና ልንገሠፅበት የተጻፈ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጾም ሲባል ከእህል ከውሃና የሕይወት ልምላሜ ከሚሰጡ ጥሉላት (ከሥጋ፤ ከወተትና ከዕንቁላል) ወዘተ ለጊዜው ተገልሎ መቆየት ብቻ አይደለም። ከምግብ የምንከለከለውን ያህል ከክፉ ሥራም ተጠብቆ መኖርን ያስተምረናል። ይህንም በሚመለከት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅ/ ያሬድ ዓይን ክፉ ከማየት፤ ጆሮ ክፉ ነገር (ሐሜትና አሉባልታን) ከመስማት፤ አንደበትም ክፉ ነገር ከመናገር ይጹም ይከልከል" ሲል በዜማው ያውጃል።

"ቢቆስልም ይድናል የተደበደበ
ምላስ ግን ይኖራል እንዳንገበገበ
ቡናስ መልካም ነበር ለሱስ የሚበጅ
ቁርሱ የሰው ሥጋ መሆኑ ነው እንጂ"

እንዳለ ባለቅኔው ከክፉ ነገርም ሁሉ በመጾም ሕይወታችን በክርስቲያናዊ ድስፕሊን እንዲለሰልስ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

በምንጾምበት ጊዜ የተራቡ ወገኖችን በማሰብ ችግረኞችን መርዳትም ሌላው የጾም ትክክለኛው ትርጉም መሆኑን ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕ·፶፰ አስፋፍቶ ገልጦታል።

ስለዚህ ጾማችንና ጸሎታችን የሠመረ ትርጉም እንዲኖረው ለተወሰነ ጊዜ ከምግብ የመከልከላችንን ያህል ከክፉ ሥራም ሁሉ ለምንጊዜውም የምንታቀብበትን መንፈሳዊ ኃይል እንዲሰጠን የእግዚአብሔር አምላካችን ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን።

አሜን

መ·ጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው



# ሰማዕታተ ኢትዮጵያ

## የ፶፪ ዓመታት የሰቆቃው ትዝታ ፡

ከአፈወርቅ አሰግድ

፲፱፻፳፱ ዓ·ም የዛሬ ፶፪ ዓመታት ትዝታ ነው። ያ ጊዜ በሀገራችን በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ፋሽስት ግፍ የፈጸመበት ወቅት ነበረ የማይረሳ ኢሰብአዊ ጭካኔ የታየበት የሰው ደም እንደጎርፍ የፈሰሰበት አብያተ ክርስቲያናት የተቃጠሉበት እናት ከልጇ ተነጥላ በእሳት የጋየችበት ሕፃናትም በሚያሰቅቅ ሁኔታ ታንቀውና በመኪና ጎማ እየተጣሉ የተጨፈለቁበት ኢትዮጵያውያን ከነሕይወታቸው ተይዘውና እጅ እግራቸውን ታስረው በውሀ ጉድጓድ ተጥለው የተገደሉበት፤ በቤታቸው እንዳሉ ከነቤተሰቦቻቸው በር ተዘግቶባቸው በንዚን ተረከፍክፎባቸው የጋዩበት ኸረ ስንቱ የኢጣሊያ ፋሽስት በኢትዮጵያ የፈጸመው ግፍ ተቆጥሮ ያልቃል ?።

ያ ሰቆቃው፤ ያ ጩኸት ያ መከራ፤ በሰፊው ጎልቶ የታየበት የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ·ም የዛሬ ፶፪ ዓመት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነበር "ኢትዮጵያውያን እ·ኤ·ዘ·አ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ·ም በዋና ከተማቸው በአዲስ አበባው ገዥ ሆኖ ከፋሽስት መሪዎቹ የተላከው ግራዚያኒ በአዲስ አበባ የሚገኙትን ነዋሪዎች ወደ ቤተ መንግሥት እንዲመጡና የምግብ የልብስና የቁሳቁስ ርዳታ የሚለገሳቸው መሆኑን ጥሪ አድርጎ ስለነበር ጀኔራል ግራዚያኒ ከሠራዊተ ፋሽስት ጋር ሆኖ በአንድ ግልጽ ቦታ ጠረጴዛውን ተደግፎ ተቀምጧል የነበረው ጥሪ ድሆችን በምፅዋት ለማስተናገድ ሳይሆን ይፈለጉ የነበሩ ሰዎች ስለነበሩና መላ የአዲስ አበባ ሕዝብ በነቂስ እንዲወጣም ትእዛዝ ስለነበር በዚያ ሳቢያ አፍኖ ለመያዝ ነበር፤

ያን ጊዜ ነበር ያልታሰበ አደጋ የተፈጠረው ጀኔራል ናዚ በአለበት ቦታ አንድ የተወረወረ የእጅ ቦምብ ፈነዳ የሞተ ሰው ግን አልነበረም ግራዚያኒና በዛ ያሉ የጦር መኮንኖች ቆሰሉ በተለይ ጀኔራል ሊዮታ የምሥራቅ አፍሪቃ አየር አዛዥ በዚሁ ቦታ በጽኑ ቆሰሉ በዚሁ ምክንያት እግሩን ተቆረጠ።

አዲስ አበባ ከተማ ተመሳቀለች ሰው መድረሻ አጣ በቤተ መንግሥቱ ቅጽር ግቢ ውስጥ የ፫፻ ኢትዮጵያውያን አስከሬኖች በዕለቱ ተቆጠሩ ማንንም ባለመለየት ጥይት በሕዝቡ ላይ ተርከፈከፈበት ይህ ግድያ የምጥ መጀመሪያ ነበር ከጥዋት እስከ ማታ ግድያው ቀጠለ ጊዜው ጨለምለም ሲል ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ የተባሉት የፋሽስት ወታደሮች እሳት አቀጣጥለውና ችቦ ይዘው ወደ ሕዝብ መኖሪያ ቤት በመጠጋት የአዲስ አበባ ከተማን በእሳት አጋዩዋት በቦምብ፤ በጥይት በሳንጃ ሕዝቡን ያለርኅራኄ ፈጁት፤ በዚህ ብቻ አላበቁም በአዲስ



www.ethiopianorthodox.org

አበባ አካባቢ ዕልቂቱ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ተሰጠ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት ደካሞች ካህናት የአካባቢው ነዋሪዎች በግፍ ተጨፈጨፉ ፡

የአዲስ አበባ ከተማ ስትቃጠል የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም እ.ኤ.ዘ.አ በሺ የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እንደከብት ተይዘው ታረዱ ደማቸው በከተማ ይቱ ውስጥ ጎርፍ ሆኖ ወረደ ።

በዚያን ጊዜ ግራዚያኒ በአንድ የኢጣሊያ ሆስፒታል መስኮት ላይ ቆሞ በምትቃጠለው የአዲስ አበባ ከተማ ዓይኑን አፍጥጦ በመ መልከት ዳግማዊ ኔሮንነቱን በግ ልጽ አሳይቷል ። በማለት አ.ጂ.ባርከር የተባለው የጦር ጋዜጠኛ ዘ.ሲቨላይዜንግ ሚሽን በተባለ መጽሐፍ ገጽ ፪፻፹፪ ፪፻፹፫ ላይ አትቶ ጽፏል ።

ከታሪክ ማኅደር በተገኘው ማስ ታወሻ ደግሞ የኢጣሊያ ፋሽስት ግንቦት ፲ ቀን ደብረ ሊባኖስ ገዳም ደርሶ ደወል ካስደወለ በኋላ የገዳሙን ዕጨጌ ተቀበሉ በማለት መነኮሳቱንና ሕዝቡን አሰባስቦ አቆያቸው በዚህ ዓይነት ግንቦት ፲፪ ቀን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ፍልሰተ አፅም በሚከበርበት ጊዜ የተሰበሰቡትን መነኮሳትና ለጸ በል የመጡትን ምዕመናን ቤተ ክርስቲያኑን በእስር ቤት መልክ በመጠቀም በረሃብና በውሃ ጥም በማሰቃየት አገር ካቆያቸው በኋላ ከምሽቱ ፪ ሰዓት ፰ ካሚዎን መኪና አቅርቦ እንደ ዕቃ አጭቆ ጭኖ ወስዷቸው በማግሥቱም ግን ቦት ፲፫ ቀን በተጨማሪ ፀ፱ ካሚ ዮን በመጫን ወደ መካነ ምቅታል ወስዶ በግፍ ፈጀቸው ።

የኢትዮጵያ ሰማዕታት ደም በዚህ ዓይነት ፈሰሰ ከገዳሙ አን

ወጣም ያሉትንም በዚያው ፈጇ ቸው ።

በአጠቃላይ ከደብረ ሊባኖስና ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የተሰበ ሰቡ ቁጥራቸው ከአምስት ሺህ በላይ የሆኑ መነኮሳትና የገዳም ሰዎች ተይዘው በረሃብና በውሃ ጥም ሲሠቃዩ ከቆዩ በኋላ ዕኩሉን ጨፌ ከሚባል ቦታ ከፊሉን ደብረ ብርሃን ወስዶ በመትረየስ ደበደባ ቸው ።

የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች እንደ መሰከሩት በአዲስ አበባ ከተማ የተሰየፉት ኢትዮጵያውያን ሰማዕ ታት ቁጥር ከ፴ ሺህ ሕዝብ በላይ መድረሱን ይናገራሉ ። ኢጣሊያ ኖች በጳጳሶቻችን በነ አቡነ ጴጥ ሮስ በነ አቡነ ሚካኤል ደም እጃቸ ውን በግፍ ታጥበዋል ።

ስለዚህ ታሪክ ተጠያቂዎች የመንበረ ጴጥሮስ ፖፖ የነበሩት እነ ፒዮስ ፲፪ኛ ለሙሶሊኒ ድጋፍ በመስጠት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዕ ልቂቱ ኸቦ ለኳሽ ሆነው በመቅረ ባቸው በታሪካችን ውስጥ ከፍተኛ የማይረሳ ቁጭትን እንዳተረፉ ይኖራሉ ።

አፈወርቅ አስገድ

## የአድዋ ድል

(ከገጽ ፲፰ የዞረ)

በሚወስደው ሜዳ እየጋለቡ የጀግ ንነት ትርኢት ሲያሳዩ የተመለ ከተ ባዕድ ምነው በኢትዮጵያ ተወልጄ ብሆን? እያለ የሚመኝ በት ጊዜ እንደነበር ከአባቶች ሲነ ገር ተያይዞ የመጣ ታሪክ ያረጋግ ጣል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤ/ክርስቲያን ጠላት ድንበር እየጣሰ ሲገባ በሚደረገው የጦር ነት ሥፍራ ሁሉ ታቦቷን በማዝ መት የጦርነት ገፈት ያልቀመሰች በት ጊዜ ባይኖርም በተለይ በዐ ድዋ የነበረው ተሳትፎ እጅግ በጣም የላቀ እንደነበር አበው ይና ገራሉ ። አሁንም ቢሆን ይህች ቤ/ክርስቲያን የሀገሪቱን ክብረ ወሰን እንዳይደፈር ወሰን ጠባቂዎ ችዋ ኃይል ፡ ብርታትና አሸናፊ ነት እንዲጎናጸፉ ሌት ተቀን ከመ ጸለይ ያቋረጥችበት ጊዜ የለም ።

አዎ መሆንም አለበት በመጀ መሪያ ሀገር ሲኖር ነውና ሃይማኖ ትና ነፃነት ሊገኝ የሚችለው ሀገር ከሌለ በሰላም በሃይማኖት በነፃ ነት የሚገኘው ጥቅም ሁሉ ሊገኝ አይችልም የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሰላም ፡ ስለጤንነትና ነፃነት ስለሀገር ፍቅር ስለወንድማማችነ ትና ስለማኅበራዊ ኑሮ ጠቃሚነት ታስተምራለች ትመክራለች አባ ቶች ለሀገራቸው ፍቅር ለነፃነት መብታቸው ፡ ለሃይማኖታቸውና ለወገኖቻቸው መሥዋዕት እየሆኑ አልፈዋል ።

ስለዚህ እኛም የሀገር ዳር ድን በር በማስከበራቸው

ወኔ ከጀግንነት ፡ ሃይማኖት ከእምነት በማስተማራቸው

ክቡራን አባቶች ክቡር ስም አላቸው

ሲወሳ ይኖራል ሕያው ታሪካ ቸው

አድዋ ላይ ሲወድቁ ሲያፈሱ ደማቸው

የአደራ መልእክት ሲጽፉ በጃ ቸው

አገርን ጠብቁ የሚል ነው ቃላ ቸው

እያልን ይህ የአባቶቻችን ፺፫ኛ ዓመት የዐድዋን ድል መታሰቢያ በዓል ስናከብር ክቡር ታሪካቸው

(ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል)



## ዐቢይ ጾም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀኖና መሠረት ከተወሰኑት ፯ አጽ ዋማት መካከል አንደኛው "ዐቢይ ጾም" በመባል የሚታወ ቀው ነው።

ይህም ጾም ከሌሎች አጽዋማት ሁሉ በሱባዔ ብዙ ዕለታት ያሉት ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የጾመው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው /ማቴ ፬ ቁ ፩—፩

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን ከኃጢአት መርገም ለማዳን ሲል ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሠላሣ ዓመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ዕለቱን ወደ ገዳም ሄደ ።

ቆሮንቶስ በተባለ ገዳም ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ጾመ በእነዚህ በጾመባቸው ቀናት ውስጥ ከዲያ ብሎስ ተፈትኖ ዲያብሎስን ድል ነሥቶአል በዚህም ላይ የኢትዮ ጵያ ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲ ያን ሊቃውንት ሲአትቱ "አዳም አባታችን በገነት ድል ተነሥቶ ነበርና በገዳመ ቆሮንቶስ ለምዕመ ናን ሁሉ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ ላቸዋል" በማለት አገናዝበው ይተረጉሙታል።

በመሠረቱ ጾም ሲባል "ጾባ ሕተ ሥጋ" (የሥጋ ግብር) ማለት ሲሆን የሰው ልጆች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ከሚአስገዙባ ቸው ነገሮች መካከል አንዱ ነው።

ያለፉት አባቶቻችን በጾማቸ ውና በጸሎታቸው ከእግዚአብ ሔር ጋር ይገናኙና ይነጋገሩ ነበር እግዚአብሔርም የወዳጆቹን የነቢ ያትና የሌሎችንም ቅዱሳን ልመና እየተቀበለ ችግራቸውን አቃሎላ ቸዋል ። ቃል በቃልም አነጋግሮአ ቸዋል /ዘጸ ፴፬ ፯—፳ ። ፩ኛ ነገ ፲፰ ፴—፵ ። ፪ኛ ነገ ፲፱ ፩—፲

በዚህም መሠረት ያለፉ አባቶ ቻችን በጾማቸውና በጸሎታቸው ከእግዚአብሔር ጋር እስከመነጋገ ርና ችግራቸውን ሁሉ እስከማስወ ገድ የደረሱት ጾማቸው ለይስሙላ ስለአልነበረ ነው ፩ኛ ነገ ፲፰ ፴

ጾም ስንል ለተወሰኑ ጊዜያት እህልና ውሃን ከመቅመስ መቆ ጠብ ብቻ ማይሆን ከቂምና ከበ ቀል ፡ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ነውረ ኃጢአት ራስን ለመጨረሻ ጊዜ ማግለል ያስፈልጋል በጾምና በጸ ሎት ከመወሰናችን በፊት በትክ ክል ልናደርገው የሚገባን የጾማች ንና የጸሎታችን የመጀመሪያ ዝግ ጅትም ይህ ነው ።

በዚህ መሠረት ማለትም ከቂ ምና ከበቀል ነፃ በሆነ ሕሊና የሚደረግ ጾምና ጸሎት ከእግዚአ ብሔር ፊት ይደርሣል እንደተ ደሞ አባቶቻችን ጾምና ልዩ ልዩ አስደናቂ ሥራዎችንም ያደርጋል አጋንንትንም ያባርራል ኃይላቸ ውንም ይሠብራል ። ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ ጾም ወጸ ሎት" (ይህ ጋኔን ያለ ጾምና ጸሎት አይወጣም ተብሎ ተጽፎአልና ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን ሲያባርረው



www.ethiopianorthodox.org

# የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ

ከሊቀ ሥልጣናት
ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

፰· “ወአሳፍኒ ወለደ ዮሣፍጥሃ ወዮሣፍጥኒ ወለደ ኢዮራምሃ ፡ ወኢዮራምኒ ወለደ አዝያንሃ” (አሣፍም ዮሣፍጥን ወለደ ፡ ዮሣፍጥም ኢዮራምን ወለደ ፡ ኢዮራምም አዝያንን ወለደ) ። አሳፍ እንደሞተ ልጁ ዮሣፍጥ ነገሠ ፡ እርሱም ፳ ዓመት ያህል ገዝቷል በዚህም ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አግኝቶ ቆይቶ ነበር ። በኋላ ግን ከአምላክ ቢሶች ከነአክአብ ጋር በመጋባቱ በነቢዩ በኢዩ ተወቅሷል ፡ እርሱም እንዲህ አለው “አንተ ለክሐዲው ታግዛለህ እግዚአብሔርንም የሚ ጠሉትን ትወዳለህ ስለዚህም ቁጣ በአንተ ላይ ነው ከእግዚአብሔር ፊት” (፪ ዜና መዋዕል ፲፱·፪) ይኸም ሁሉ ሁኖ አልተመለሰም ፡ እንደገናም ከአካዝያስ ጋር ግንኙነት አደረገ በዚህም ምክንያት በነቢዩ በአልዓዛር ተወቅሷል እንዲህ ሲባል “ከአካዝያስ ልጅ ጋር አንድነት አድርገሃልና እግዚአብሔር ሥራህን አፈረሰ ፡ መርከቦችም ተሰበሩ ፡ ወደጠርሴስም ይሔዱ ዘንድ አልቻሉም” (፪ ዜና መዋዕል ፳·፴፯) ። ለቤቱና ለዘሩ ጥፋት የሚያመጣውን ሥራ ሁሉ ይሠራ ነበርና ።

ኢዮራምም አዝያንን ወለደ ፡ ከዮሣፍጥ በኋላ የነገሠው ኢዮራም አባቱን ተከትሎ ከአክአብ ቤተሰብ ጋር ተጋባ። በሚስቱም ፍቅር ተስቦ ጣዖትን አመለከ ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ጣዖት ማምለክን በብዛት አስገባ ፡ የኢዮራም የመጀመሪያው ከባድ ጥፋት ነፍስን ማስጠፋቱ ነበር በዚሁም ሥራው ፮ቱን ወንድሞቹን አስገደለ ። ከዚህም በኋላ በሀገሩ ሁሉ ብጥብጥና ፈሪሃ እግዚአብሔርን ማጣት ሆነ ። በዚህም መልክ ፰ ዓመት ብቻ ነግሦና ሞተ ፡ ለእርሱም ምንም ክብር ሳይሰጠው በነገሥታቱም መቃብር ሳይቀበር ቀረ ። ወዲያው ልጁ አካዝያስ ከአታሊያ የአክአብ ልጅ ከሆነችው ሴት የተወለደ መንግሥቱን ያዘ ። አካዝያስ በእሥራኤል በኢዩ ከተገደለ በኋላ የአካዝያስ እናት አታሊያ የተባለ ችው ልጆቹን ሁሉ ገደለቻቸው ፡ ነገር ግን ኢዮአስ የተባለው የአካዝያስ ልጅ ብቻ ተርፎ ነበር ፡ በአካዝያስ እህት በዮሼቫ ምክንያት ። ኢዮአስም ነገሠና ፴ ዓመት ገዛ ፡ ግን ወዲያው ጣዖት ማምለክ ጀመረ ፡ በዚህም ክፉ ሥራው አምላክ ተቆጣውና በራሱ አሽከሮች ተገደለ ። እርሱም እንደሞተ ልጁ አሜስያስ የተባለው ነገሠና ፳፱ ዓመት ገዛ ፡ እርሱም እንዲሁ ተገደለ ። በዚህን ጊዜ አካርያስ ወይም አዝያን የተባለው ነገሠ ፡ ወንጌላዊ ማቴዎስ ግን የአራም ልጅ አድርጐ አቅርቦታል ።

አካዝያስን ኢኮንያንን ፡ አሜስያስን ሳይቆጥር ወንጌላዊው አልፏቸው ሔዷል ፡ ምክንያቱም መምለኪያነ ጣዖት ናቸው በማለት ነው፡ ከአክአብ ጋር በመጋባታቸው ኢየሩሳሌምን በጣዖት ሞልተዋት ነበርና ። እንግዲህ ደህና ስም የላቸውምና ስማቸው ሊነግ ዘራቸው ሊወሳ በቅዱስ ወንጌል ሊጻፉ አይገባም ብሎ እንደተዋቸው ይገመታል ።

፱. “ወአዝያንኒ ወለደ ኢዮአታምሃ ፡ ወኢዮአታምኒ ወለደ አካዝሃ ወአካዝኒ ወለደ ሕዝቅያስሃ”

(አዝያንም ኢዮአታምን ወለደ፡ ኢዮአታምም አካዝን ወለደ ፡ አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ) አዝያንም አባቱ አሜስያስ ከሞተ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት መልካም አደረገ፡ ነገር ግን የመንግሥቱን ክብር ለመጠበቅ ሲል በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የድፍረት ሥራን ሠራ ማለት እንደ ሊቀ ካህናቱ ከመቅደስ ገብቶ ዕጣን ያጥን ጸሎት ያሳርግ ጀምር ። በዚህ የድፍረት ሥራው እግዚአብሔር ተቆጥቶ በለምጽ ቀጣው ፡ እርሱም በዚሁ አፍር ከቤቱ እንደ ዋለ በዚሁ ለምጽ ሞተ ። ልጁ ኢዮአታም በእግሩ ተተክቶ ነገሠና ፲፮ ዓመት ገዛ ፡ በእግዚአብሔር ፊትም ሞገስን አገኘ ።

ኢዮአታምም አካዝን ወለደ ፡ አካዝ ፲፮ ዓመት ነገሠ በእግዚአብሔር ፊትም በደለኛ ሁኖ ተገኘ ፡ ማለት ጣዖት ሲያመልክ ተገኝቷልና በዚህ ኃጢአቱም ፈጥኖ ተቀሠፈ ፡ ሲሞትም በነገሥታት የመቃብር ቦታ የመቀበር ዕድል ሳይገጥመው ቀረ ። በዚህ ንጉሥ ጊዜ የተነሣው ነቢይ ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ ስለነበር እርሱም ከፍተኛውን ምሥጢር ገልጦ “ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ” ብሎ የተናገረ ነው ። (ኢሳ ፯·፲፩—፲፪)።

አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ ፡ ሕዝቅያስም ከእሥራኤል ነገሥታት መካከል ቅድስና የነበረው ንጉሥ ነበር ፡ እንደ ቅድመ አያቱ እንደ ዳዊት አምላኩን ለማገልገል፡ ለማስደሰትም ይጥር ነበር ። እርሱም ፳፱ ዓመት ነግሦ ቆይቶ አረፈና ልጁ ምናሴ ተተካ ።

፲· “ወሕዝቅያስኒ ወለደ ምናሴሃ ፡ ወምናሴኒ ወለደ አሞጽሃ ፡ ወአሞጽኒ ወለደ ኢዮስያስሃ”

(ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ ፡ ምናሴም አሞጽን ወለደ ፡ አሞጽም ኢዮስያስን ወለደ) ። በደጉ ንጉሥ በሕዝቅያስ እግር የተተካው ከአብራኩም የተከፈለው ምናሴ ይሠራው የነበረ ተግባር ሁሉ ለአባቱ ለሕዝቅያስ ምግባርና ሃይማኖት ተቃራኒ ነበር።የሕዝቅያስ ልጅ ሁኖ በሕዝቅያስም እግር ተተክቶ የመጨረሻ የርኩሰትንና የክፋትን ሥራ ያለ ቅሬታ እየፈጸመ ሰውንም ሁሉ ያሳዝን ነበር ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አላገኘም ፡ በአባቱ ጊዜ የነበረውን የእግዚአብሔርን አምልኮት አስቀርቶ የጣዖት አምልኮትን ተካ ፡ በኢየሩሳሌም ላይ እንደገና የጣዖትን አምልኮ አስፋፋ ። በዚህ ክፉ ሥራው ሁሉ እግዚአብሔር ተቆጣና ተማርኮ በሰንሰለትም ታሥሮ ወደ ባቢሎን በተወሰደ ጊዜ ሲያውቅ በድፍረት ይሠራው የነበር ኃጢአት ተከሠተለት ጥፋቱንም ሁሉ ተገነዘበ ። በዚህ ጊዜ ተጸጸተና ንስሐ በመግባቱ ነፃነት አግኝቶ ወደ ሀገሩ ተመልሷል ። ይኸ ሰው ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር በመመለሱ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ የቅድስና ኑሮ እየኖረ ዕድሜ ጠግቦ ፶፭ ዓመት ነግሦ ኑሮ አርፏል ። እንዲያውም ለተነሣህያን ሁሉ ጸሎት የሚሆን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ይቅርባይነትንም የሚገልጥ ጸሎተ ምናሴ እያልን በስሙ የምንጠራውን ጸሎት ትቶልን ሙቷል ።

ምናሴም አሞጽን ወለደ ፡ ከምናሴ በኋላ የተተካው ልጅ አሞጽ በእግዚአብሔር ዘንድ በደለኛ ሁኖ ተገኘ ፡ ስለዚህ ብዙ ሳይቆይ በነገሠ በ፪ ዓመቱ ተቀሰፈ ፡ ሞቱም አሰቃቂ በሆነ መንገድ ተፈጸመ ፡ በአሽከሮቹ እጅ ተገደለ። ይኸ ስም ግን አምን ፡ አሞጽ እያለው ይገኛል ።

አሞጽም ኢዮስያስን ወለደ አሞጽ እንደተገደለ ሕዝቡ በአንድነት ተነሥቶ ገዳዮቹን ተበቀሏል ፡ ወዲያውም ልጁን ኢዮስያስን አነገሡታል ። ይኸም ኢዮስያስ የተባለ ንጉሥ ፈቃደ እግዚአብሔር እየፈጸመ እንደ አያቶቹ እንደነ ዳዊት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ቆይቷል ፡ እንዲያውም ከመጨረሻዎቹ ከእሥራኤል ነገሥታት ቅዱስ ሁኖ የተገኘው ይኸው ንጉሥ ነበር ። በቃልም በሥራም ፈቃደ እግዚአብሔርን እየፈጸመ ከኢየሩሳሌም ምድር አምልኮ ጣዖትን አስወጥቶ የሙሴ ሕግ በትክክል እንዲነገር አድርጓል ።

## በአንድ ደብር ...

(ከገጽ ፳፬ የዞረ)

ርሳል ሕይወተ ነፍሱንና ሕይወተ ሥጋውን ከማጣት የደረሰው ከገንዘብ ፍቅር የተነሣ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የቤተ ክህነት ሠራተኞችን የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ካህናትን በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ሰብስበው መመሪያ በሰጡበት ወቅት የገንዘብ አያያዝ ልክና መልክ እንዲኖረው በገንዘብ ነክ ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች በጥንቃቄ እንዲሠሩ አሳስበዋል ።

ቅዱስነታቸው እየተዘዋወሩ የአንዳንድ አድባራትንና ገዳማትን የገንዘብ አያያዝ ሲመለከቱ በአንድ ደብር አራት ገንዘብ ያገኙ መሆናቸውን ገልጸው እንደዚህ ያለው አሠራር ለገንዘብ መባከን ታላቅ በርን የሚከፍት ስለሆነ እርማት እንዲደረግበት መመሪያ ሰጥተዋል ። በመቀጠልም በአንዳንድ ተንኮለኞች ሰዎች ምክንያት ደጋግ ካህናት እንዳይወቀሱ በቤተ ክርስቲያናችን አካባቢ ንትርክ ሊኖር አይገባም ፡ ችግር እንዳይደርስበት ማንኛውም ሰው እንዲጠብቀው የተሰጠውን ገንዘብ ሳያባክን በመጠበቅ ቤተ ክርስቲያንን የማገልገል መንፈሳዊ ግዴታ አለበት ብለዋል።

---

የነበሩት አባቶቻችን ከክፋ ድርጊት ነፃ በሆነ ልቡና ወደ እግዚአብሔር የሚአቀርቡት ልመና ከራሳቸው አልፎ ሌሎችንም የሚአድን ነበር ።

ይህንንም በትክክል ሊአስገነዝበን የሚችለው በ፩ኛ ሳሙ ምዕ ፲፪ ቁ፳፫ ላይ “እኔ ለእናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ” በማለት ነቢዩ ሳሙኤል የተናገረውን ስናስብ ጾማችንና ጸሎታችን በንፁህ ሕሊና የሚደረግ ከሆነ ለሀገርና ለወገን ሁሉ የሚረዳ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ስለዚህ በታላቁ በጌታችን የጾም ወራት እርስ በእርሳችን ፍቅርን እንደሸማ ተጎናጽፈን ስለራሳችንም ሆነ ስለሌሎች ሰላምና ሕልውና ወደ እግዚአብሔር ዘወትር እንጸልይ ።

የ፲፱፻፸፩ ዓ/ም የጌታችን ጾም መግቢያ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የካቲት ፳፯ ቀን ስለሆነ ሁላችንም ለመጾም መዘጋጀት ይገባናል።

መሪ ጌታ ኤፍሬም በየነ





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከመ/ሉሌ መልአኩ

## ሐ/ የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና ያፈራቻቸው መንፈሳውያን አባቶችና መምህራን

ክክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ እስክንድርያ ውስጥ ሙዚየም የተባለው ከፍተኛ የግሪክ (የአሕዛብ) ትምህርት ቤትና የአይሁድም ትምህርት ቤቶች ስለነበሩ ይህችው ከተማ የአሕዛብና የአይሁድ ሊቃውንት (ፈላስፎች) መፍለቂያ፡ መናኃሪያና የዕለት (የትምህርት) ማዕከል ነበረች ።

በዘመነ ክርስትናም በቅዱስ ማርቆስ ተመሥርታ ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን ለተቀበሉ ሰዎች (ንኡሳን ክርስቲያን) የክርስትናን መሠረተ እምነት ተረድተው እንዲጠመቁ የሚረዳ የሰንበት ትምህርት መስጫ (ማስተማሪያ) ሆና ቆየች ። በሁለተኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ግን በፓንጼኖስና በኃይኛቹ ተጠናክራ በመቋቋም በክርስቲያኑ ዓለም ከፍ ያለ ዝናን አትርፋ ነበር። ይህችው ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃ በማቅረብ የወንጌልን ትምህርት በዓለም ያስራፉ ዝነኛ ሊቃውንትንና የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በማፍራት ፡ ብዙ ምእመናንንም በማስተማር ለክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጋለች ። ስለዚህ ከአሕዛብና ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ከተቀበሉት መካከል ከፊሎቹ በዕውቀት የበሰሉ ምሁራን ስለነበሩ የነሱን መንፈሳዊ ትምህርት ፍላጎት ለማርካት ፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና የወንጌል መልእክተኞችን በከፍተኛ ደረጃ ለማሠልጠን በማቀድ የትምህርት አሰጣጡ ደረጃ ከፍ ከፍ እያለ በመሄዱ በክርስቲያኑ ዓለም የመጀመሪያዋ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመሆን በቃች ። ሆኖም በዘመኑ ለንኡሳን ክርስቲያን የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት መስጫ ለሆኑ ት/ቤቶች ክርስትና በተስፋፋባቸው ሀገሮች ተከፍተው ነበር ። ነገር ግን ለወደፊት ሰፋ አድርገን እንደምንመለከተው በከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ የእስክንድርያን ት/ቤት ልትወዳደር የቻለችው የቅዱሳት መጻሕፍትን የአንድምታ ትርጓሜ በመቃወም የነጠላ (የቃል በቃል) ትርጉምን የምትከተለው የአንጾኪያ መንፈሳዊ ት/ቤት ብቻ ነበረች ።

የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ዋነኛ ዓላማዋ ከነበረው ከመንፈሳዊ ትምህርት በተጨማሪ እንደ ሎጂክ ፡ ፊሎዞፊ ፡ ሪቶሪክ ፡ ታሪክ፡ ሳይንስ ፡ አስትሮኖሚ ፡ ሒሳብ የመሳሰሉ ዓለማዊ ትምህርቶችንም ትሰጥ ነበር ።

ምሥጢራቸው የረቀቁ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርቶች ፍች ለመረዳት የእስክንድርያ ትምህርት ቤት "የቅዱሳት መጻሕፍት የነጠላ ትርጉም ከበስተጀርባው ምሥጢራዊ ፍች አለው" በማለት አንድምታ (አሊጎሪክ ፡ ቲፖሎጂ) በተባለው የአተረጓጎም መንገድ (ስልት) ትጠቀም ነበር ። የአሊጎሪክ ትርጓሜ ስልት የተጀመረው በግሪክ ፈላስፎች ነበር ይባላል ። ከአይሁድም ሊቃውንት መካከል ፊሊእ ዘእስክንድርያንና መሰሎቹ ብሉይ ኪዳንን በአሊጎሪክ መንገድ ተርጉመዋል ። ከክርስቲያኖችም ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ፡ አርጌኒስ ወዘተ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአሊጎርኪ ስልት ተርጉመዋል ። ሐዋርያው ጳውሎስም በመልእክታቱ አንዳንድ ቦታዎች ውስጥ በአሊጎሪክ አተረጓጎም ተጠቅሟል (ገላ ፬፡፳፬ ፡ ፩ ቆሮ ፲፡፲) ።

የእስክንድርያ ት/ቤት ለክርስቲያኑ ፡ ዓለም እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ድረስ መንፈሳዊ ትምህርትን በስፋትና በጥልቀት ስትሰጥ ከቆየች በኋላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ለመጀመሪያ ጊዜ በእምነት ምክንያት ለሁለት ከተከፈሉበት ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ እየተዳከመች ሄደች ። እንድትዳከምና እንድትጠፋ ያደረጉአትም ያን ጊዜ ግብጽን በቅኝ ግዛት ያስተዳድሩ የነበሩት የሁለት ባሕርይ እምነት ተከታዮች የቢዛንታይን (የቁስጥንጥንያ) ነገሥታት ናቸው ። እነሱም የተዋሕዶ (የአንድ ባሕርይ) እምነት ተከታይ የነበሩ ኮፕቶችን ከማሳደድና ከመጨፍጨፍ ተግባራቸው በተጨማሪ ትምህርት ቤቷን ዘግተው በውስጧ የነበሩትን መጻሕፍት ዘርፈው ወደ ቁስጥንጥንያ ወሰዱ ። የኮፕት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከዘረፋ የተረፉትን መጻሕፍት ሰብስበው ትምህርት ቤቷን ከእስክንድርያ ዋዲ·ኤል·ናትሩም በሚባለው በረሃማ ቦታ ወደሚገኘው የቅዱስ መቃርዮስ ገዳም በማዛወር መጠነኛ ትምህርት እንድትሰጥ አድርገው ነበር ። ሆኖም እስከ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ውሱን በሆነ ሁኔታ መንፈሳዊ ትምህርትን ስትሰጥ ቆይታ በገዳሙ አካባቢ ከነበሩ ዘላኖች በመነከሳቱ ላይ ይሰነዘር በነበረው ዝርፊያና ግድያ ምክንያት ቀስ በቀስ ደብዛዋ ጠፋ ።

እላይ እንደተመለከትነው እስክንድርያ ውስጥ ትምህርት ቤቷ ከተዘጋበት ከአምስተኛው እስከ አሥራ ዘጠነኛ ክፍለ ዘመን ድረስ የግብጽ ካህናት መንፈሳዊ ዕውቀት ተዳክሞ ከቆየ በኋላ በአምላክ ፈቃድና እርዳታ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ቄርሎስ አምስተኛ በ፲፰፻፺፫ ዓ/ም ትምህርት ቤቷ እንደገና በተጠናከረ ሁኔታ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ደረጃ ካይሮ ውስጥ ተከፍታ ካህናትንና መምህራንን በማስተማርና በማሠልጠን ላይ ትገኛለች ። ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተላኩ ደቀ መዛሙርትም በዚችው ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል ። አሁንም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ይገኛሉ ።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የእስክንድርያ ት/ቤት ከመዘጋቷ በፊት በመንፈሳዊ ትምህርት ኮትኩታ ካፈራቻቸው አያሌ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና መምህራን መካከል ቅዱስ አትናቴዎስ ፡ የእስክንድርያው ቀሌምንጦስና ቄርሎስ ፡ አርጌንስ ፡ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፡ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ወዘተ ይገኙባቸዋል።

ከመጀመሪያዎቹ የትምህርት ቤቷ መሥራች ከወንጌላዊው ማርቆስ ቀጥሎ ጁስቱስ ፡ ኢውማኒእስ፡ ማርያኑስ ፡ ፓንዲኖስ ፡ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ፡ ቴዎግኖስቱስ ፡ ፒኤርዮስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እውሩ ዲዲሞስ ወዘተ በተከታታይ የትምህርት ቤቷ መሪና አስተማሪ በመሆን በትጋት አገልግለዋል ።

ከነሱም መካከል ፓንጼኖስና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ትምህርት ቤቷን ከመምራት ተግባራቸው በተጨማሪ በሕብረት ሂኤሮግሊፍ የተባለውን ጥንታዊውን የግብጽ ስዕል መሳል ፊደል የተካ አዲስ ፊደል አዘጋጁ ። ይኸውም ሃያ ሁለት በሚሆኑ በግሪክ ፊደል በመጠቀም ሰፊው የሀገሬው ተወላጅ ሕዝብ የሚጠቀምበት ለጽሕፈትና ለንባብ ቀናና አመች የሆነ አዲስ የቅብጥ ቋንቋ ፊደል በማዘጋጀት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ምትክ ያልተገኘላቸው ሰባት ድምጽ ሰጭ የሆኑ የራሳቸውን ጥንታዊ ፊደላትም ከሃያ ሁለቱ የግሪክ ፊደላት ጋር ጨምረው አስገብተዋል ። እንዲሁም ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን ካህናትና ምእመናን አንብበው በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉ በማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቅብጥ የተረጐሙ እነሱ ናቸው ።

የቅብጥ ቋንቋ የተለያዩ ዲያሌክቶች (የጐሳ ቋንቋዎች) አሉት ከነሱም ዋናዎቹ በሔሪክ የተባለው የታሕታይ ግብጽ ዲያሌክትና ሳሂዲክ የተባለው የላእላይ ግብጽ ዲያሌክት ናቸው ። መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመው በነዚሁ በሁለቱ ዲያሌክቶች ነው ።

ግብጾች ለብዙ ዘመናት በቅብጥ ቋንቋ ሲነጋገሩ ፡ ሲጽፉና የለት ከዕለት ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ከኖሩ በኋላ ሀገራቸው በዐረቦች እጅ ስለወደቀች ከ፯፻፲፮ ዓ/ም ጀምሮ ማንኛውም ዜጋ ዐረብኛ እንዲናገርና እንዲጽፍ ፡ የመንግሥት ሥራም በዐረብኛ ብቻ እንዲናወን ተደረገ ። ስለዚህ ቅብጥ ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄዱ ከአሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሥርዓተ ቅዳሴ መፈጸሚያ ብቻ ሆኖ ቀረ ። ሕዝቡም በስፋት በዐረብኛ መናገር ፡ መማርና መጻፍ ስለጀመረ ከጊዜ በኋላ የቅብጥን ቋንቋ እየረሳ ሄደ ። አሁን በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ የሚፈጸመው ቦሔሪክ በተባለው የቅብጥ ዲያሌክት ነው ። ሆኖም የቤተ ክርስቲያኒቱን መገልገያ መጻሕፍት ይዘትና ፍች ምእመናን በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉ በማሰብ አብዛኞቹ በቅብጥና በዐረብኛ ጐን ለጐን ተጽፈው የተዘጋጁ ናቸው ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፱ የዞረ)

ህም ስንልህ የአንድ መጽሔት ዋጋ ፩ ብር የአንድ ጋዜጣም ዋጋ ፲ ሳንቲም ሲሆን መላኪያውም የያንዳንዱ ፳፰ ሳንቲም ይከፈላል ይህንን ከከፈልክ ማኅበርተኛ ለመሆን ትችላለህ ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

# የአድዋ ድል

ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ የታሪክ ቦታዎች አሉአት ከነዚህም አንዱ ዐድዋ ነው የዐድዋ ከተማ የሚገኘው በትግራይ ክፍለሀገር በሰሜናዊ ክፍል ነው ይህ ከተማ ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ 25 ኪ/ሜትር ያህል ራቅ በሎ የሚገኝ ነው ።

ይህ ታሪካዊ ቦታ በአክሱም ዘመነ መንግሥት የመናገሻው ክልል ነበር እየተባለ ይነገርለታል በዚሁ ጽሑፋችን የዐድዋን ታሪክ ለማዘከር የፈለግነው የካቲት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ/ም አፄ ምኒልክ ከጀግኖች ኢትዮጵያውያን ጋር ፋሽስት ኢጣልያን የደመሰሱበት ዕለት ስለሆነ "የዐድዋ ድል" እየተባለ ታሪኩ ሲነገር የሚኖር መሆኑን ለመግለጽ ነው ።

ዐድዋ በመስቀለኛ መንገድ ላይ የተቆረቆረ ከተማ ነው ይኸውም ከሽሬ ተነሥተን ወደ አዲግራት ስንጓዝ በዚሁ ከተማ መሐል እናልፋለን እንዲሁም ከተምቤን ተነሥተን ወደ አሥመራ ስናልፍ መሐል ለመሐል አቋርጠን የምንጓዘው በዚሁ በዐድዋ ከተማ ነው። ስለዚህ ፋሽስት ጠላታችን ሀገራችን ኢትዮጵያን ለመውረር ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ ከአሥመራ ተነሥቶ የመረብን ወንዝ ተሻግሮ የጦር አውድማ ለማድረግ የፈለገው በዚሁ ከተማ ነበር ።

ስለሆነም ፋሽስት ሀገራችን ኢትዮጵያን ለመውረር ባደረገው በዚሁ ሙከራው የነበረው ዝግጅት ከጀግናው አፄ ምኒልክ ዝግጅት ጋር ሲነጻጸር እንደሰማይና ምድር የተራራቀ ነበር ጣልያን ጉልቄ መሥፈርት በሌለው ጥይት ፡ ቦምብና መትረየስ መድፍና (አእሮፕላን) መሪና ልዩ ልዩ የሰው ዘር ማጥፊያ መሣሪያ ነበር የተሰለፈው ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የውጭ መሣሪያ በመጠኑ ቢኖረውም ጦርና ጐራዴ ነበር የያዘው ።

ይህ ታሪክ በጎልያድና በዳዊት መካከል እንደነበረው ሁኔታ የሚመሳሰል ነው ። ጎልያድ ቁመቱ ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ በራሱ ላይ የናስ ቁር የደፋ አምስት ሺህ የናስ ስቅል የሚመዝንና በእግሮቹም ላይ የናስ ገምባሌ ያደተገ ፡ የናስም ጭሬ ትከሻው ላይ የተሸከመ ስድስት መቶ ስቅል የሚመዝን ብረት የጦሩ የቦ (ዘንግ) የያዘ ከፍልስጥኤማውያን መካከል የታወቀ ጀግና ነበረ ዳዊት ግን ገና ሕፃን ብላቴና ከመሆኑም በላይ አምስት ድቡልቡል ድንጋዮች የድንጋዮቹ መቀመጫ አንድ ኮሮጆ በጎቹን ከነጣቂ ተኩላ የሚጠብቅበት አንድ ወንጭፍ ብቻ ነበረው ። ዳዊት በጎልያድ ፊት እንደትንኝ ነበር የሚታየው ዳዊት ግን በሕዝበ እግዚአብሔር ፊት እንደአምባ ይታይ ነበር። ጎልያድ ከላይ በተጠቀሰው ግዙፍ ሰውነቱ በያዘው የጦር መሣሪያው ይመካ ነበር ዳዊት ግን በኃያላን ኃይል በእግዚአብሔር ብቻ ይመካ ነበር ዳዊትና ጎልያድ ፊት ለፊት ቀርበው ጦርነት በከፈቱ ጊዜ ዳዊት ጎልያድን በአንዲት ድቡልቡል ድንጋይ ግንባሩን መትቶ ጣለው ከዚያም ዳዊት በጎልያድ ላይ ወጥቶ የገዛ ሰይፉን አንሥቶ አንገቱን ቆርጦ በሳኦል ፊት ግዳይ ጣለው ።

በጎልያድ የተመሰለው ፋሽስት ኢጣልያ በዳዊት የተመሰሉት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በዐድዋ ጦርነት የገጠሙት እንደፋሽስት በጦራቸውና በጎራዴአቸው ተመክተው ሳይሆን አሸናፊው እግዚአብሔርን ጋሻና መከታ በማድረግ ነበር ። ዳዊት ከእምነት ጋር ጠላቱን ጎልያድን ቆራርጦ እንደጣለው ሁሉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንም ዐድዋ ላይ ጠላታችን ፋሽስት ኢጣልያንን ቆራርጠው የጣሉት እምነት ከጀግንነት፡ ወኔ ከሀገር ወዳድነት አስተባብረው በመያዛቸው ነው ።

ዐድዋ ላይ የተካሄደው ታሪካዊ ጦርነት ከጀግኖቹ አባቶቻችን ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ካህናትና ዲያቆናት መምህራንና መዘምራን የየአጥቢያቸውን ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በመያዝ ዘምተዋል ። ጀግኖቹም ታቦቱና ካህናቱን በማስቀደም ሰልፋቸውን አሳምረው ጠላትን ሲገጥሙት ጉልበቱ ተብረከረከ ኃይሉ ደከመ መድረሻ አጣ ተብከነከነ የተቀረውም የኀፍረት ሸማውን ተጐናጽፎ በመጣበት መንገድ ተመለሰ ።

በዐድዋ ታሪካዊ የጦርነት ድል ላይ የርእሰ አድባራት አክሱም ጽዮን ታቦታትና የአድዋ ዐድባራት ታቦታት እንዲሁም የአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ መናገሻ ቅ ጊዮርጊስ ታቦት ተገኝተው በተራዳኢነታቸው ለጀግኖች ኢትዮጵያውያን አባቶች ከለላ ሁነውላቸው ውለዋል ።

ጠላታችን ፋሽስት ሞትና ውርደት ተቀብሎ ከሀገራችን በተባረረ ወቅት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የጦር ልብስ ለምዳቸውን ደርበው ጋሻቸውን አንግበው ጦራቸውን እየሰበቁ በፈረሶቻቸው ላይ ተቀምጠው ወደ እንዳባ ገሪማ

(ወደ ገጽ ፲፪ ዞሮአል)



# መንፈሳዊ ሥነ ምግባር

መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ባሕርይንና ጠባይን ብቻ ሣይሆን ግብረገብነትም ስለሆነ ወንድማማችነትንና አብሮ መኖርን ያጠቃልላል ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በ፩ኛው መልእክቱ በም.፲፭ ቁ ፴፫ የጻፈውን ብናነብ "አትሣቱ ክፉ ባልንጀራ መልካሙን አመል ያጠፋል ። በጽድቅ ንቁ ኃጢአትንም አትስሩ" ሲል እናገኘዋለን ። ሐዋርያው እንዳለው ሰዎች መልካም ባልንጀራ ሲኖራቸው መልካም ጠባይና ጥሩ ባህርይ ይኖራቸዋል ። አበው የሚመስሉት አንድ ታላቅ ምሳሌ አለ ይኸውም ከበቅሎ ጋር የዋለች ጊደር እርግጫ ተምራ ወደ ጋጧ ገባች የሚል ነው አንድን ሰው ማንነቱን ለማወቅ ከፈለግን ከማን ጋር እንደሚውልና ባልንጀራው ማን እንደሆነ አጥብቆ መረዳትና ማስተዋል ያስፈልጋል ።

እንደ ሊቃወንቱ አባባል ሰው አካባቢውን ይመስላል አብሮ ከሚውለው አብሮ ከሚኖረው ጋር ይመስላል ። በዚህ አኳኋን መልካም ከሆኑት ባልንጀሮቻችን ዘንድ ተለይተን ጥሩ ጠባይ ከሌላቸው ሰዎች ጋር ጓደኞች ብንሆን መልካም ጠባያችን እንደሚበላሽና በዚህም የተነሣ የተለያየን ሆነን እንድንኖር ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል ።

ይህ መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ወይም ሞራል ወይም ጠባይ በውጭ ሰውነታችን ብቻ የምናሳየው መሆን የለበትም ነገር ግን በውስጡ ሕይወታችን ተለውጦ ሊታይ ይገባዋል ለምሳሌ የዘመናችን አነጋገር አለ ይኸውም ወደ ሕንድ ስትሄዱ ሕንዶችን ወደ አሜሪካን ስትሄዱ አሜሪካኖችን ወደ እንግሊዝ ስትሄዱ እንግሊዞችን በጠቅላላው ወደ ሄድክበት ሀገር ሁሉ የአገሮቹን ሰዎች ምሰል የሚል የፍልስፍና አነጋገር አለ ምናልባት ይህ አባባል ለጊዜው ይጠቅም ይሆናል ። ዘለቄታ ግን የለውም ይሁን እንጂ መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ከዚህ ጋር መመሳሰል ቀርቶ በምንም አይቀራረብም ምክንያቱም መምሰልን ሣይሆን መሆንን ስለሚጠይቅ ነው ።

በተጨማሪም መንፈሣዊ ሥነ ምግባር እንደዚያ ማይሆን ወይም የማስመሰል ሕይወት ሳይሆን አልፎ ተርፎ የውጭውን ሕይወት የሚለውጥ መሆን አለበት ይህ ከሆነ ብዙ ጊዜ የውስጥ ሕይወታችን የውጭ አቋማችን ያንፀባርቀዋል ሰው በውጭው አቋም ዓለምን መስሎ ቢታይ ያ ሁሉ ጊዜ የሚያማየው የውስጥ ሕይወቱን ነው ። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ም. ፲፪ ፡ ፩ — ፪ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው ። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጐና ደስ የሚያሰኝ ፍፁምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" ብሏል ።

እንደአለውም ዓለም በበኩሉ የራሱ ለውጥና ተሐድሶ አለው ። የሰዎችን ጠባይና ባህሪ ሲለውጥ እና የዋለን እንዳንዶቹን ከታማኝነት ወደ ክህደትና ወደ ገንዘብ ስርቆት ሌሎቹን ደግሞ ወገናቸውን ጠልተው ራሣቸውን ወደው የግል ጥቅም እንዲያሣድዱ ያደርጋቸዋል ። የተረፉትን ደግሞ, ጥንት የነበረውን መልካም ጠባያቸውን ለውጦ እና ክፉ ባህሪ እንዲቀስሙ አድርጎ በወዳጆቻቸውና በዘመዶቻቸው ላይ እንዲጨክኑ በሐሰት እንዲመሰክሩና በአድልዎ እንዲፈርዱ ይገፋፋቸዋል። ይህ እንግዲህ ዓለም የሚሰጠው ለውጥ ነው እንዲህ ያለው ለውጥ ሕይወትን አሮጌ ከማድረግ በቀር አዲስ ሕይወትንም አያመጣም የመንፈስ ለውጥም አያስገኝም ።

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ግን ወደዚህ አለም የመጣው ሰዎችን ሊያገለግል እንጂ ሊያገለግሉት አይደለም እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አለመጣምና "በሚለት ማዘዝ ፡ ማገልገል አዲስ ጠባይ ሰጥቶ በአካሄዳችሁም በሥራችሁም እኔን ምስሉ ብሎ አዟቸዋል የሥነ ምግባር ለውጥም ትርጉምም ይህ ነው እና ።

ለዚህም መረጃ እንዲሆነን አንድ የግሪክ ፈላስፋ ተማሪዎቹን እኔን ምስሉ ሲል የተናገረውን ምክር እናቀርባለን ፈላስፋውም "ተማሪዎችን እኔን ምስሉ እላቸው ይህንንም ስል ልጅ ወላጆቹን መልክ ፡ በቀለም ፡ በቁመት ፡ በውበት ፡ መስሏቸው እንደሚወለደው አይደለም ። እንዲህ ያለው ድርጊት ከዘርና ከደም የሚወረስ የተፈጥሮ ግዴታ በመሆኑ አያስደንቅም እኔንም ምስሉ ያልኳችሁ ከእኔ ባገኛችሁት ትምህርት እንደ እኔው መምህር እንድትሆኑና ከፍ



www.ethiopianorthodox.org

ተኛ ድግሪ አግኝታችሁ አስተዳዳሪ ወይም ባለሥልጣን እንድትሆኑ ብቻ አይደለም ። ይህንን በጥናት ብዛት ማንም የሚያገኘው የድካም ፍሬ በመሆኑ ልማድ ነው እኔን ምሰሉኝ ያልኳችሁ ግን በቃል ፡ በሥራ ፡ በእምነት ነው እግዚአብሔርም ሰውን እንደመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፈጥረው ያለው በአፍንጫችን ፡ በዐይናችን ፡ በፀጉራችን ፡ እንደንመስለው ሣይሆን በሥነ ምግባራችን ፡ በርህራሄ ሌላውን ለማገልገል እንደንመስለው ነው ” አለ ይባላል ።

ይህ አባባል በውስጡ ሰውነታችን ፈጣሪያችንን እንደንመስል ያብራራል ስለዚህ ብዙውን ኃጢአትም ሆነ መልካም ኑሮ ለውጥም ይሁን ቅድስና በጠቅላላ ማንኛውም ሥራ የሚጀመረው ከውስጥ ባለው ሕይወታችን ነው ። የውጭ ሕይወታችን ብዙውን ጊዜ የሚያንፀባርቀው የውስጡ ሕየወታችንን ነው ስለዚህ አንድ ሰው የውጭ ሕይወቱን በማየት የውስጡ ሕይወቱ ምን ዓይነት እንደሆነ ለመረዳትና ለማወቅ ይቻላል ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በውጭ ሊያስመስሉ ይችሉ ይሆናል ። እውነተኛ ሰውነታቸው ግን በውስጥ ሊደበቅ ይችላል ። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ዝምተኛ መስለው ይታያሉ ። የተፈጥሮ ጠባያቸውንም ለማመሳሰል ይሞክራሉ ። ነገር ግን ጓደኞቻቸው ጠባያቸውን ለማወቅ ሲሉ እየኮረኮረ ያስቋቸዋል ። ጠባያቸውንም እንዲገለጥ ያደረጉባቸዋል ። በዚህ ጊዜ ሲቆጡ ትክክለኛ ሰውነታቸው ሲገለጥ ይታያሉ ። ያ ዝምታቸው ያ ትእግሥታቸው ሁሉ የማስመሰል አርተፊሻል ነበር ማለት ነው ። መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ግን እንደ ወርቅ የተፈተነ እንጂ የማስመሰል አርተፊሻል ሕይወት አይደለም ። ይህም ሊሆን የሚችለው በውስጡ ያለው ሕይወታችን በመንፈስ ሲለወጥና ሲታደስ በውጭ ብዙ የሥራ ፍሬ እና የተሐድሶ ለውጥ ይታይበታል ። ለመንፈሳዊ ሥነ ምግባር የሚረዱን ሶስት አርእስተ ጉዳዮች አሉ ። አንደኛ የእግዚአብሔር ቃል ሁለተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ሶስተኛ ሕሊናችን ነው ።

መንፈሳዊ ሥነ ምግባር በሰው ሕይወት ውስጥ መስረፅ የሚጀምረው ሰው የእግዚአብሐርን ቃል አምኖ ሲቀበልና ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ሲወለድ ነው ። ይህንንም በፈፀመ ጊዜ የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ይጀምራል ። ክርስቶስንም የመምሰል ሕይወት መኖር ይጀምራል ። ለመንፈሳዊ ሥነ ምግባር አፈፃፀም ደንበኛ ምሳሌያችንና ልንከተለው የሚገባን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ። ከዚህ በኋላ በገላትያ ም፭ ቁ፳፪ ፳፫ ያሉትን የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወታችን እናፈራለን ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን ምሰሉኝ ባለው መሠረት ከውሃና ከመንፈስ የተወለደው በሥራው በአካሄዱም ክርስቶስን እየመሰለ ይሄዳል ።

ይሁን እንጂ ስለ መንፈስ ፍሬ በምንነጋገርበት ጊዜ የመንፈስ ፍሬ እያደገ የሚሄድ ስለሆነ ምናልባት ብዙ ጊዜ በአንዳንድ አማኝ ሕይወት ውስጥ ቶሎ አይታይ ይሆናል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለሆነ ውሎ አድሮ በተግባር መገለፁ ስለማይቀር በትእግሥት መጠባበቅ ያሻል በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ከሌላቸው የመንፈስ ፍሬ ላይኖራቸው ይችላል ። ይህንንም የሚያጡበት ዋናው ምክንያት በሆነ ባልሆነው ይቆጣሉ ። ፍቅር ይጐላቸዋል እርስ በርሳቸው ይጣላሉ ። ስለዚህ ሲያጡ ሲበሳጩ ይታያሉ የመንፈስ ፍሬ የሚታየውና ለውጥ የሚገኘው እነዚህ ሁሉ ከሰው ሕይወት ውስጥ ጨርሰው ሲጠፉ ነው ።

የመንፈስ ፍሬ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ማንኛውም አማኝ በእግዚአብሔር ቃል ሲያድግና ሲመሠረት ነው በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንፈስ ዕለት ዕለት በልቡ እንዲጋባ ሲፈቅድለት ነው ። እነዚህን ሁለቱን ስጦታዎች ማንኛውም አማኝ አንድ አድርጐ መያዝ ይፈለግበታል ። ሊቃውንት የሚመስሉት ምሳሌያዊ አነጋገር አለ ይኸውም “ቃል ብቻ አትሁን ትደርቃለህ ፡ መንፈስም ብቻ አትሁን ትፈነዳለህ ነገር ግን ቃሉም መንፈሱም በውስጥህ ከኖረ ታድጋለህ” የሚል ነው ። ላቀረቡትም ምሳሌ መረጃ ሲሰጡ አንድ ህጻን ለማሣደግ ብንፈልግ ውሀ እንዳይጠማ ክልክለን በየቀኑ እህል ብቻ እየመገብን ሆዱን ብንጐስረው ወይም እህል ክልክለን ውሃ ብቻ እየጠጣን ሆዱን በውሃ ብንሞላው የመኖርም ፡ የማደግም እድል የለውም ። እንዲያድግና እንዲኖር ከተፈለገ በየቀኑ ሁለቱንም ማግኘት ይኖርበታል ይላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ አትክልትም ሆነ ዛፍ እንዲያድግ ከተፈለገ አፈር ያስፈልገዋል ውሃም ያስፈልገዋል ።

ሰውም መንፈሳዊ ሥነ ምግባር እንዲኖረው ከተፈለገ የሚያስፈልገው ቃል ብቻ አይደለም የእግዚአብሔርም መንፈስ ያስፈልገዋል እነዚህ ሁለቱ በሰው ሕይወት ውስጥ ካሉ የመንፈስ ለውጥ ያገኛል ፡ ያድጋል ፡ የመንፈስ ፍሬም ያፈራል ።

ምን ጊዜም የአማኝ ሕይወት መንፈሳዊ ሥነ ምግባር ሊኖረው ይገባል የሚባለው በክርስትና ሕይወቱ ያደገና የበሰለ ሰው ሲሆን መልካም አኗኗር ሊኖር ይቻላል ምክንያቱም የመንፈስ ፍሬ በሕይወቱ ስለማታይ ነው ክፋዎችንና መልካም ዛፎችን ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ተብሏል ስለዚህ ሰዎች የሚያውቁን በመስበካችን ብቻ አይደለም በመናገራችንም ብቻ አይደለም በአኗኗራችን ጭምር ነው ። ስለዚህ አኗኗራችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ። ብዙ ሰዎች የሚናገሩትን በሥራ ላይ ስለማያውሉት ፡ መልካም ሥነ ምግባር ስለሌላቸው መልካም አኗኗርም ስለማይኖራቸው የሚናገሩትም ሆነ የሚያስተምሩት ፡ የሚሰብኩት ብዙ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም ። ስለዚህ መንፈሳዊ ሥነ ምግባር የሚያስተምረን ከመናገራችን በፊት አስቀድመን በአኗኗራችንና በአካሄዳችን መልካም ምስክርነት ለሰዎች እናሳይ የሚል ስለሆነ ከመስበካችንና ከመናገራችን በፊት በአኗኗራችንና በሥራችን ለሰዎች ምሳሌ እንሁን ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---

## የአድዋ ድል

(ከገጽ ፲፱ የዞረ)

በእያንዳንዳችን ልብ እንዲሳልና የእነርሱንም ክቡር ዓላማ እየተከተልን ተልእኮአችንን ለመፈጸም እንድንችል የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁልን ።

ሊ. ትጉሃን ገ ክርስቶስ
ኃ/ማርያም

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊትና ታሪካዊት መሆኗን የታሪክ መዛግብት ቢያስረዱና ምስክርነታቸውንም በጉልሕ ጽፈውት ቢገኝም ከዚህ የታሪክ ጉዞ ጋር የተለያዩ የልማት ሥራዎች አብረው ተያይዘው የመጡ መሆናቸውንም የታሪክ መዘክሮች ያስገነዝባሉ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይ በገጠር ያሉት አብያተ ክርስቲያናት መታወቂያቸውና መለያቸው የአካባቢው አፀዶች በመሆናቸው ማደሪያ የሚያጡ እንግዶችና ተማሪዎች ከሩቅ ሆነው ተመልክተው ጉዞ አድርገው ዕረፍት የሚሹት በዛፎች አማካይነት ነው ።

አብዛኞዎቹ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አስተምረውና ተምረው የተገኙትም በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ ከአሉት ዛፎች በመሆናቸው ሊቃውንቱ ትምህርታቸውን ከልማት ሥራ ጋር በማቀናጀት አብረው ሲሠሩና ሲያሠሩ ኖረዋል ። አሁንም የገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን መምህራን ይሠሩበታል ያሠሩበታል ።

በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የራሷን አመራር በራሷ አሠራር ማካሄድ ከጀመረችበት ዕለት አንስቶ በሰበካ ጉባኤ አደራጅነት በአገልጋዮች ካህናት ሠራተኞችነት የልማት ሥራዎች ተግባር በይበልጥ ትኩረት በማግኘቱ በማኅሌትና በሰዓታት ፡ በቅዳሴና በውዳሴ ብቻ የተወሰነው ሰውነት ለልማት ሲፋጠን ማየቱ ታላቅ የምሥራች ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እንደብዛታቸው መጠን መኑ ዘይተክል ወይነ ወኢይበልዕተክሎ ፍሬውን የማይበላ ላምን ጠብቆ ወተትን የማይጠጣ ማን ነው ፩ኛ ቆሮ ፱ ፯ እያሉ ቢያስተምሩ በየአሉበት አብያተ ክርስቲያናት ቢተጉና ቢያስተባብሩላቸው አልፈው ሌሎችን ለመርዳት እንደሚችሉ አያጠራጥርም ።

ከመቀበል ይልቅ የሚሰጡ እንደሚበልጡ መጽሐፋችን ስለሚያስተምረን ከተረጅነት ወደ ረጂነት የሚደርሱበትን መንገድ በመቀጠል አንድነታቸውን አጠንክረው በልማት ሥራ ከተሠማሩ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ህላዌና የራሳቸውን ኑሮ አሻሽለው የሌሎች ዓለማት አብያተ ክርስቲያናት ካህናት በደረሱበት የዕድገት ደረጃ እንደሚመጥቁ ግልጽ ነው።

የልማት ሥራዎች ስንል ዛሬ ተቋቁመው በመገናኛ ዘዴዎች ተገልጸውና ተነግረው ታይተው የሚጠፉትንም አብረን ማሰብ ይኖርብናል ። በአንድንድ ቦታ ያለው ጥናት ገንዘብ ይዋጣና ሥራ ከተጀመረ በኋላ የወጣውንም ወጭ ሳይተኩ አራሙቻ ተጭኖት የሚቀር የልማት ሥራ እንዳለም አይዘነጋም ።

ከዚህ ለየት በማድረግ ትኩረት ልንሰጠውና ለወደፊትም ዘለቄታ በማግኘት ተሠርቶ ተረጅ በማስገኘት ውጤት ይሰጣል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት በክርስቲያንዊ ተራድኦ መምሪያ በኩል በሚሰጠው የርዳታ ገንዘብ ከሌላው ዓመታት ወዲህ የ፲፮ እህጉረ ስብከት በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ



www.ethiopianorthodox.org

ጉባኤ ስብሰባ ይዘዋቸው የሚመጡት የልማት ሥራዎች ጉልሕ ማስረጃዎች ናቸው ። በዚህም አጠቃላይ ስብሰባ የመጡት የልማት ሥራዎች በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተመርቀው ከተከፈቱ በኋላ ሲጐበኙ ሠራዎችን ብቻ ሳይሆን ተመልካቾችንም ጭምር አስደስተዋል።

አብዛኛዎችም በተመጣጣኝ ዋጋ እየገዙ የቤት ዕቃዎችንና ጌጣጌጦችን ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ጥቅም እንዲውሉ አድርገዋል ።

በዚህም የተግባረ እድ ሥራ የተለያዩ ሥራዎች ከየሀገረ ስብከቶች መቅረባቸው ቢገለጽም በተለይ በአንጋፋነት በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የጎፋ ጥበበ እድ አቅርቦአቸው የነበሩት የቤተ ዕቃዎችና የፋምሊ አልጋዎች ጥራታቸውና ብቃታቸው ጉልሕ ማስረጃዎች ሆነው ታይተዋል ። ለእነዚህ ሁሉ የልማትና የተግባረ እድ ሥራዎች በየወቅቱ እየተጠናከሩ እንዲሔዱ በየአህጉረ ስብከቱ የተቋቋሙት የካህናት ማሠልጠኛዎች ኃላፊነት ስለአለባቸው ከአሰለጠኑ በኋላ በሥራ ላይ መዋላቸውን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል ።

ሌላው ለልማት ሥራ ተብሎ በርዳታ የተገኘው ገንዘብ በወቅቱ ለልማት ሥራ ከዋለ በኋላ በአንዳንድ ትኩረትና ቁጥጥር ስለማይደረግበት ከመልማቱ የመጥፋቱ ዜና ለሰሚም ክፍል ያሳዝናል ለወሳጅም ያስገምታል ያስወቅሳል ያስከስሳል ዜና አቅራቢውም "በአንድ አፍ ሁለት ምላስ" እንደ ሚባለው ይሆንና በመድረክ ላይ የሚናገረውና የሚያቀርበው ሪፖርት ሁሉ ሁልጊዜ ተደማጭነት ሊያገኝ አይችልም ።

ይህ ዓይነቱ የልማት ሥራ አስቀድሞ ከመጀመሩ በፊት የዚህ ልምድ ባላቸው ሰዎች ተጠንቶና ተዘጋጅቶ ቢሠራ ውጤቱ በየጊዜው እየቀጠለ እንደሚሔድ አያጠራጥርም ።

ልማት ስንል በግብርና በረከትና በተግባረ እድ ብቻ የሚገኘውን ሳይሆን ካህናትን በሞያ ማሠልጠን ልማት ነው ምእመናንን በቃለ እግዚአብሔር ማነፅ ልማት ነው ።

ስለዚህ የልማት ዓይነቱ ብዙ መሆኑ ቢታወቅም የዚህ ልምድ ዓላማ በየአህጉረ ስብከቶች የሚካሔዱትን የልማት ሥራዎች እየተከታተለ ማስተዋወቅና እንዲበረታቱ ማድረግ ስለሆነ የልማት ሥራዎች የአሉአቸው አህጉረ ስብከቶች ሁሉ የሥራ ውጤቶቻቸውን በዚህ ዓምድ እንዲገልጹ እንጋብዛለን ።

ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም

# ዜና ሊቃወንት

## የሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ ዜና ዕረፍት

ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ በታች ጋይንት ወረዳ በምትገኘው ቅድስት ቤተ ልሔም የድጓ ምስክርና የደብሯ ዋና አስተዳዳሪ ሁነው ሲአገለግሉና ሲአስተምሩ ቆይተው በተወለዱ በ፷፩ ዓመታቸው ሐምሌ ፲፯ ቀን ፸፯ ዓ/ም ከዚሕ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ስመ ጥሩ የሆኑት ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ ከአባታቸው ከብላታ መንግሥቱ መርሻ ከእናታቸው ከወ/ሮ ታሪክ ቢተው በ፲፱፻፲፮ ዓ/ም ጥር ፳፮ ቀን በደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም ሰበካ ክልል ተወለዱ።

እድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ከታወቁት መምህር የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም መሪጌታ ኃይሉ እሸቱ ከተባሉት ከፊደል እስከ ዳዊት ተምረዋል ከዚያም ከብፁዕ አቡነ አብርሃም የዲቁና ማዕርግ ተቀብለው በደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም ለሦስት ዓመታት ያህል በዲቁና አገልግለዋል ።



ሊቀ ምሁራን ጥበቡ እኒህ ነበሩ

ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ በዲቁና አገልግሎት ማይወሰኑ በአላቸው የትምህርት ፍላጐት ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሒደው ከታወቁት መምህር ከወ/ሮ ገላነሽ የቅኔ ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ በይበልጥ ለማጠናከር ወደታወቁት መምሕር ወደ ማዕበል ፈንቱ በመሔድ እስከ መምህርነት የሚያአበቃ ሙያ ተምረው ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመልሰዋል ።

የድጓው ምስክር ጥበቡ መንግሥቱ በቅኔ ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ የዜማ ትምህርት ለመማር በተወለዱበት ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በፋርጣ ወረዳ አዛውር ኪዳነ ምሕረት ከታወቁት መምሕር ከመሪጌታ ጀምበር ወንድም ከጾመድጓ እስከ ድጓ ድረስ አጠናቀው ከአወቁ በኋላ በሊቦ አውራጃ ደብረ ተክለ ሃይማኖት በመሔድ ከመሪጌታ ትሕትና ለሦስት ዓመታት ያህል የአቋቋም ትምህርት ተምረው ዚቅና መዝሙር ጽፈው የአቋቋሙን ትምህርት አጠናቀዋል ።

ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በጋይንት አውራጃ ላይ ጋይንት ወረዳ የዝማሬ መዋሥዕት ምስክር ሁና ከምትገኘው ወደ ዙር አባ ጽርሐ አርያም ገዳም በመሔድ ዝማሬ መዋሥዕት ከመሪጌታ መርአዊ ተምረው አስመስክረውና ጽፈው ወደ ትውልድ ቦታቸው ተመልሰው አገልግሎት ሲሠጡ ከቆዩ በኋላ የዜማ መዲናና ምስክር ሁና ከምትገኘው ወደ ቅድስት ቤተ ልሔም ሔደው የድጓ ምስክር ከሆኑት ከአለቃ አምሣሉ ተምረው ድጓ ለማስመስከር ቀደም ብለው ጽፈዋቸው የነበሩትን ጾመ ድጓ ምዕራፍና ድጓ ይዘው ለምስክርነት የሚያበቃ ሙያ ስለነበራቸው አለቃ አምሣሉ ከዚሕ ዓለም በሞት ሲለዩ በድጓ አስመስካሪዎችና በማሕበረ ካህናቱ ተመርጠው የድጓ ምስክር ለመሆን በቁ ።

ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ በመልካም ሥራቸውና ሙያቸው መምሕራቸው አለቃ አምሣሉ መርሻ የእርሳቸውን ወንበር የሚተኩ መሆናቸውን ስለአወቁ ልጃቸውን ወ/ሮ እቴናት ፈታሒ የተባሉትን ለጋብቻ ፈቅደውላቸው በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም በሕግ ተወሰነው በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ሥርዓት ጋብቻቸውን ፈጽመዋል።

ስመ ጥሩው አለቃ አምሣሉ መርሻ በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ከዚሕ ዓለም በሞት ሲለዩ ሊቀ ምሑራን ጥበቡ መንግሥቱ የቀለም አባታቸውን ኃዘን ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን በሚአዘው መሠረት ለአንድ ዓመት ያህል በተጠባባቂነት ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፷ ዓ/ም ዋና የድጓ ምስክር ሁነው ተሹመዋል።

ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ የድጓ ምስክር ሁነው ሲሾሙ ካባ ቀሚስና ሙሉ ሽልማት አግኝተዋል ። እኒሕ የታወቁ ሊቅ በአላቸው ሙያና ዕውቀት በሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ኃላፊነት ታትሞ የምሑራንና የደቀ መዛሙርቱን ችግር ያቃለለውን አምስቱ ጸዋትወ ዜማ ጽፈው አቅርበው እንዲታተም የአደረጉ ምሑር ነበሩ ።

ሊቀ ምሕሩን ጥበቡ በሕይወት በነበሩባቸው ዘመናት የጻፉአቸው መጻሕፍት ፡

ሀ· አራት ሙሉ ድጓ ለ· ስምንት ጾመ ድጓ ሐ· ስድስት ምዕራፍ መ· ሦስት ዝማሬ መዋሥዕት ሠ· አምስት የጎንደር አባ ጃሌ ዚቅ ረ· ሁለት የሰንበት መዝሙራት ሰ· ሁለት የቅኔ አገባብ ሸ· አራት የድጓ አንቀጽ ናቸው ።

ሊቁ ጥበቡ በአላቸው ሙያ ከ፲፱፻፷ እስከ ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ድረስ በ፲፯ ዓመታት ውስጥ ፫፻፸፯ የድጓ አድራሾችን በአዕምሮ አጐልምሰው በዕውቀት አሰልጥነው ምስክር ወረቀት ሰጥተው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

ሊቀ ምሑራን ጥበቡ መንግሥቱ ወ/ሮ እቴናት ፈታሒን በሕግ አግብተው የአሥራ ሁለት ልጆች አባት ሲሆኑ በተወለዱ በ፷፩ ዓመታቸው ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ በታላቋ ደብር በቅድስት ቤተ ልሔም በደብሩ ካህናትና የድጓ አድራሾች በአካባቢው የሚገኙት የአብያተ ክርስቲያናት መምሕራንና ካህናት በተገኙበት የጸሎተ ፍትሐቱ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ዘመድ ወዳጆቻቸው በተገኙበት ተፈጽሞአል ።

መ· ፍሥሐ ባንተ

### ማረሚያ

ቁጥር ፩፻፴፫ ገጽ ፲፰ ታህሣሥ ወር ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በወጣው ትንሣኤ መጽሔት "ሴቶች በክርስቲያናዊ ሕይወት" ጽሑፍ የባለ ታሪኳ እማሆይ በዝናሽ ባህሩ ፎቶግራፍ በስህተት ሳይወጣ ከመታለፉም በላይ ታሪኩን ያቀረቡት ስም ሳይጠቀስ ታልፎአል ።



ስለዚህ ታሪኩን ያቀረቡት አቶ አድማሱ ዘውዴ ሲሆኑ ባለታሪኳ እማሆይ በዝናሽ ባህሩ እኒህ ነበሩ።



www.ethiopianorthodox.org

# በአንድ ደብር አራት ገንዘብ ያገኙ

መዝገብህ በአለበት በዚያ ልብህ ይኖራል ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮናል አባቶቻችንም ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ይላሉ ይህ ሁሉ የገንዘብን ተፈላጊነት የሚያስረዳ ነው አንዳንድ የሳይንስ ሊቃውንትም ገንዘብን ከሰውነት ደም ሥር ጋር በማነፃፀር ሲናገሩ ለሰውነት ሕይወት የሚሆነው ደም በሚገባ እየተዛወረ ሥራውን ሲሠራ እንደሆነ ገንዘብም ለሰው ልጅ መኖር ከፍተኛ አገልግሎት ሰጭ የደም ሥር ነው ይላሉ ።

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የሚበላውን እህል ፡ የሚጠጣውን ውሀ ፡ የሚለብሰውንና የሚኖርበትን ቦታ ሁሉ አዘጋጅቶ ሲያበቃ በኋላ ሰውን መፍጠሩ ሰው ያለገንዘብ አለመኖሩን ለማስረዳት ሲል ነው እንደዚህም ሲባል ሰው ገንዘብ ይዞ ከእናቱ ማኅፀን አይወለድም ተወልዶ ከአደገ በኋላ ግን ወጥቶ ወርዶ ሠርቶ ገንዘብ ያገኛል ። በገንዘቡም ይበላል ፡ ይጠጣል ፡ ይለብሳል ፡ ያጌጣል ። ካልበሉ እሬሳ ካልለበሱ እንስሳ እንደሚባለው ደክሞ ባገኘው ገንዘብ ፍላጎቱን በማሟላት ይኖራል እንደዚህም ሲባል ሳይወጡ ሳይወርዱ ፡ ገንዘብ ያለ ድካም ሊገኝ አይችልም በብዙ ድካም የተገኘውን ገንዘብ ደግሞ በማይገባ መንገድ እያወጡ ማባከን ተገቢ አይደለም ገንዘብ በሚገባ ከሥሩበት በምድራዊው ዓለም ከሰው ጋር ያፋቅራል ያስማማል ፡ ለሰማያዊው ኑሮም መንገድን ከፍቶ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ያስገባል ።

ገንዘብን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚሰጠው መልካም ሥራ እንዲሠራበት ነው እንጂ እንደ ጣዖት እንዲያስቀምጠው አይደለም በማቴዎስ ወንጌል ተመዝግበው የምናገኛቸው ሦስት ሰዎች አሉ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ታሪኩን ብንመለከተው የገንዘብንና የሥራን ፡ የስንፍናንና የትጋትን ውጤት ግልጽ አድርጐ ያስረዳናል ። ማቴ ፳፭ ፡ ፲፬ — ፴

በገንዘባቸው ክፉ ሥራ በመሥራት የተጐዱ ብዙ ሲሆኑ መልካም ሥራ ሠርተውም የእግዚአብሔር ወዳጆች ተብለው ይገኛሉ ለምሳሌ የአብርሃምንና የኢዮብን ታሪክ ስንመለከት ሁለቱም ባለጸጐች ነበሩ ፡ በገንዘባቸው ግን አልተመኩበትም አብርሃም ቤት የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእኔ አይደለም በማለት ቤቱን ከፍቶ ያለፈ ያገደመውን የወጣ የወረደውን መንገደኛ እየተቀበለ ያበላና ያጠጣ ነበር ለታረዘው ልብስን ለመንገደኛው ስንቅን ከመስጠት ወደኋላ አይልም ነበር ።

ኢዮብም በሁሉም የበለጸገ ሲሆን የሚሠራው መልካም ሥራ እንደ አብርሃም ነበር ፡ ከደግነታቸውም የተነሣ የእግዚአብሔር ወዳጆች የእግዚአብሔር ባለሟሎች ተብለዋል ። ለማስረጃ ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ በገንዘባቸው መልካም ሥራ የሠሩ እነርሱ ብቻ አይደሉም ሌሎችም ይገኛሉ ።

በእነሡ አንጻር ደግሞ በፍቅረ ንዋይ "ገንዘብ በመውደድ" የተጐዱ አያሌ ናቸው ከብዙዎቹ አንዱ ነዌ የተባለው ባለጸጋ ነው ይህ ባለጸጋ ልልበስ ቢል የፈለገውን ዓይነት ልብስ የሚያገኝ ልብሳ ልጠጣ ቢል አማርጦ ለመብላትና ለመጠጣት የማይገደው ሰው ነበር ።

በእርሱ ደጅ ወድቆ ፍርፋሪ እየተመገበ የሚኖር አልዓዛር የሚባልም በቁስል ደዌ የተመታ ሰው ነበር አልዓዛር ለውሾች ከሚጣለው ፍርፋሪ በስተቀር ምንም አያገኝም ነበር ይህ ባለጸጋ እንደተንደላቀቀ ለሁልጊዜ ለመኖር አልቻለም ሞት የማይቀር ዕዳ ነውና ሞተ በዚያን ጊዜ ነፍሱን ተቀብለው የወሰዲት መላእክተ ጽልመት ናቸው አልዓዛር በሞተ ጊዜ ነፍሱን ተቀብለው የወሰዲት መላእክተ ብርሃን ናቸው ።

ባለጸጋው ነዌ በመከነ ደይን እንዳለ አልዓዛርን በተድላ በደስታ ተቀምጦ ተመለከተ አባቴ አብርሃም ሆይ እባክህ አልዓዛርን ላክልኝ ጣቱን ከውሃ ነክሮ አንደበቴን ያቀዝቅዝልኝ ዘንድ በዚህ የመከራ እሳት ተቃጥያለሁና ሲል ለመነው አብርሃምም መልሶ ከዚህ ያሉ ወደእርሱ ከእርሱ ያሉ ወደዚህ እንዳይተላለፉ በመሃከል ታላቅ ገደል ስላለ አይቻልም አለው ።

ባለጸጋው ይህ ካልተቻለ አምስት ወንድሞች አሉኝ እነርሱም ወደዚህ መከራ እንዳይገቡ ሂጄ ላስተምራቸው ፍቀድልኝ አለው እርሱም መልሶ መምህራንንና መጻሕፍትን ይስሙ እነርሱን ካልሰሙ ግን ከሙታን ተለይተህ ሄደህ ብትነግራቸው አይስሙህም በማለት በዚያው እየተሠቃየ እንዲኖር አስረድቶታል ። ሉቃስ ፲፮ ፡ ፲፱ — ፴፩ ካላወቁበት ገንዘብ ያስወቅሳል ያስከስሳል ሕይወተ ሥጋንም ነፍስንም ከማሳጣት ይደ

(ወደ ገጽ ፲፭ ዞሮአል)



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቀኖናዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ ... ን እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ... ት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org